አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ



## ፪ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፪(2)ኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


አዘጋጆች

ሙሉቀን ፈንታ መኮንን

አሻግሬ ግባቱ ገበየሁ

አዲስዓለም አሸኔ ለማ

ገምጋሚና አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

የጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ



አቀማመጥ እና ስዕል

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

© የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

**ምስጋና**

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፒሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ **ዘላለም ሙላቱ** ፣

እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ አድማሱ ደቻሳ** ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ዳኛው ገብሩ**፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ሳምሶን መለሰ** ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ **ወ/ሮ አበበች ነጋሽ** ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ **አቶ ሲሳይ እንዳለ** ፣ ለቴክኒክ አማካሪ **አቶ ደስታ መርሻ** ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ **የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን** ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

መግቢያ....................................................IV

ምዕራፍ አንድ

ልብስ....................................................1

ምዕራፍ ሁለት

ወቅቶች....................................................12

ምዕራፍ ሶስት

ታሪኮች....................................................24

ምዕራፍ አራት

የአትክልት ቦታ....................................................34

ምዕራፍ አምስት

የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ....................................................46

ምዕራፍ ስድስት

ባህላዊ ሙዚቃ....................................................59

ምዕራፍ ሰባት

መልካምሥነምግባር....................................................70

ምዕራፍ ስምንት

የምግብ አዘገጃጀት....................................................80

ምዕራፍ ዘጠኝ

ዲጅታል ቁስ....................................................89

ምዕራፍ አስር

የዱር እንስሳት....................................................98

ዋቢ ጽሑፎች....................................................107

አባሪዎች....................................................108

# መግቢያ

## ለተጠቃሚዎች

ይህ መፅሐፍ የ፪ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መፅሃፍ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መፅሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መፅሃፍ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

## መርህ አንድ

ተማሪዎች ስዕሎችን በመመልከት ተረቶችንና ታሪኮችን የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

## መርህ ሁለት

ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ (ምንባብ) በሚገባ በማዳመጥ ያዳመጡትን ታሪክ (ምንባብ) በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ተግባር ለማድረግ ተከታታይነት ያለው የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡

## መርህ ሶስት

ተማሪዎች የቋንቋው ተተኳሪ ፊደላት የሚወክሏቸውን ውስብስብና ሞክሼ ፊደላትን ተገቢ የሆነ የፊደላት አሰዳደር ሥርዓት በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ፡፡

## መርህ አራት

ተማሪዎች በውስብስብና ሞክሼ ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## መርህ አምስት

ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የተዘውታሪ ቃላቱን ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን ይረዳሉ፤ የቃላት ዕውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሑፍ ሐሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

## መርህ ስድስት

ተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን(ተረቶችን) እና ሌሎች ፅሑፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ በመስራት ማዳበር ይተበቅባቸዋል፡፡

# ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጆች(አሳዳጊዎች)

ልጆቻችን የቋንቋውን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የእኛና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፤ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግምት ውስጥ በማስገባት በቤት ውስጥ ልጅዎን ሲያግዙም፣

፩. ለልጅዎ የተለያዩ ታሪኮች፣ ተረቶች ወዘተ ይንገሯቸው ወይም ያንብቡላቸው፡፡

፪. ለልጅዎ የነገሯቸውን ታሪክ(ተረት) መልሰው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

፫. በተማሪ መፅሃፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችና ተግባራት በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

፬. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲያዳምጡ፣እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

፭. ልጆችዎ መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች እና ሌሎችን በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎን ይወጡ፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
## ልብስ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የምታዳምጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ትለያላችሁ፡፡
- ከተሰጣችሁ ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ባለ ሶስት ሆሄ ቃላትን ታጣምራላችሁ፤ ትነጥላላችሁ፡፡
- ሆሄያትን አቀናጅታችሁ ቃላት ትጽፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ልብስና መስሪያዎቹ





### ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች እናንተ ምን አይነት ልብስ ለብሳችኋል?
2. ከላይ ያሉትን ስዕሎች በማየት ስለምን እንደምታዳምጡ ገምቱ?

### አዳምጦ መናገር

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. ልብስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ኩታ ከምን ይሰራል?

### ቃላት

፩. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የጎደሉትን ፊደላት በምሳሌው መሰረት በጽሑፍ አሟሉ፡፡

ምሳሌ፡- ል__ስ = ልብስ

1.____ራብ　　　　3.____ጠላ

2. ቀሚ___　　　　4. ጃ______ት

፪. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን በማቀያየር ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ለበሰ = በሰለ፣ሰለበ

1. ቀለበ = ________
2. ቀጠነ = ________
3. ማለዳ = ________
4. በደለ = ________
5. ልብስ = ________

## ሞክሼ ፊደላት

**ሞክሼ ፊደላት** የምንላቸው በፊደል ገበታ ላይ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው፣ በድምጽ ግን ተመሳሳይ የሆኑ ፊደላት ናቸው።።

### በፊደል ገበታ ላይ ያሉ ሞክሼ ፊደላት

| ሀ | ሐ | ኀ |
|---|---|---|
| ሠ | ሰ | |
| አ | ዐ | |
| ጸ | ፀ | |

፩. በምሳሌው መሰረት የሞክሼ ፊደላትን ዝርያዎች ፃፉና አንብቡ።።

| ምሳሌ | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| | ሀ | | | | | | | ጸ | | | | | | |
| | ሐ | | | | | | | ፀ | | | | | | |
| | ኀ | | | | | | | | | | | | | |

፪. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሞክሼ ፊደላትና ዝርያቸውን የያዙትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- አየለ ዐይኑ ስለታመመ ሀኪም ቤት ሄደ፡፡

- አየለ
- ዐይኑ
- ስለታመመ
- ሀኪም

1. ሰይድና ህልውና አስፋልት ሲሻገሩ በዜብራ ላይ ነው፡፡
2. ፀዳለ ወላጆቿን ታከብራለች፡፡
3. ማኅበረሰቡ ባለው ኃይል ቢተባበር ሀገር ይለማል፡፡

## ንባብ



## ቅድመ ንባብ ጥያቄ

1. ስዕሉን በመመልከት ስለምን እንደምታነቡ ገምቱ?
2. ምን ምን የልብስ አይነቶችን ታውቃላችሁ?

### የበዓል ልብስ

ዕለቱ የጥምቀት ዋዜማ ነው፡፡ በአካባቢው ልዩ ልዩ አልባሳትን የለበሱ ሰዎች ይታያሉ፡፡ ሕሊና ያሸበረቀ የሐበሻ ቀሚስ ከነጫማው ለብሳለች፡፡ አባቷ ደግሞ ነጭ በነጭ ለብሰው ቀይ ጃኖ በላዩ ላይ አገልድመዋል፡፡ አባትየው ልጃቸው ህሊናን በመያዝ በዓሉን ለማክበር ወጡ፡፡ ህሊና ድንገት የትምህርት ቤት ጓደኛዋን አየችው፡፡ ጓደኛዋ መሐመድ ጀለቢያ ለብሶ በውጭ በር ላይ ቆሟል፡፡ ቆቡን እየነካካ የበዓሉን ድባብ ይመለከታል፡፡ ሕሊናም መሐመድን ከአባቷ ጋር በዓይን አስተዋወቀችው፡፡

## አንብቦ መረዳት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. እነሕሊና የሚሄዱት የጥምቀት በዓልን ለማክበር ነው፡፡
2. የህሊና ጓደኛ ሴት ናት፡፡
3. በጥምቀት በዓል የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት ይለበሳሉ፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ በግል ደጋግማችሁ ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ ከዚያም ድምጻችሁን በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ቃላት

፩. በ “ሀ” ስር ላሉት ቃላት ከ “ለ” ስር ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዕለት | ሀ. አየ |
| 2. ዋዜማ | ለ. ያጌጠ |
| 3. ያሸበረቀ | ሐ. ከዋናው በዓል አስቀድሞ የሚገኝ ቀን |
| 4. ተመለከተ | መ. ባልንጀራ |
| 5. ጓደኛ | ሠ. ቀን |

፪. የሚከተሉትን ምስሎች በሚገባ በመመልከት የምስሎችን መጠሪያና ያላቸውን ቀለም በምሳሌው መሰረት ጻፉ፡፡

| መገለጫ |  ምሳሌ |  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መጠሪያ | ሹራብ | | | | | |
| ቀለም | ቀይ | | | | | |

## ☞ ውስብስብ ፊደላት

ውስብስብ ፊደላት ማለት ሁለት ድምጾችን በአንድ ላይ አጣምረው የያዙ ፊደላት ናቸው::

ለምሳሌ:- "ሉ" + "ዋ" = ሏ

| ውስብስብ ፊደላት በቅደም ተከተላቸው | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሧ | ፏ | ሷ |
| ቋ | ቧ | ቷ | ቿ | ኗ |
| ኳ | ኟ | ዟ | ዧ | ዷ |
| ጓ | ጧ | ጯ | ጿ | ፏ |

፩. ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ውስብስብ ፊደላትን ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

፪. ተማሪዎች በቡድን በመሆን በምሳሌው መሰረት ከውስብስብ ፊደላት ውስጥ አራቱን መርጣችሁ ቃላት በመመስረት ለመምህራችሁ አሳዩ::

ምሳሌ:- ፏ = ፏጭ፣ ጸጉሯ፣

1.______ = ______________  3.________=______________

2.______= ______________  4.________= ______________

## ☞ ማጣመርና መነጠል

፩. የሚከተሉትን ውስብስብ ፊደላት ነጣጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሟ = ሙ-ዋ

1. ሿ = __________  4. ጯ = __________
2. ዧ = __________  5. ፏ = __________
3. ፗ = __________

፪. የሚከተሉትን ፊደላት በማጣመር ውስብስብ ፊደላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ሱ + ዋ = ሷ

1. ጡ + ዋ =__________  4. ቡ + ዋ =__________
2. ሩ + ዋ =__________  5. ዡ + ዋ =__________
3. ዱ + ዋ =__________

## ✍ ጽሕፈት

፩. መምህራችሁ የሚያሳዩዋችሁን ድርጊታዊ ገለጻ በሚገባ በመመልከት ድርጊቱን በቃላት ጻፉ።

ለምሳሌ፡-



መብላት

፪. መምህራችሁ የሚነግሯችሁን ቃላት በሚገባ አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ፡፡

:: ?

ሥርዓተ ነጥብ ማለት ስሜትንና አገላለፆችን በጽሑፍ ውስጥ አጉልቶ የሚሳይ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ. <u>አራት ነጥብ (፡፡)፡-</u> ይህ ስርዓተ ነጥብ ዓረፍተ ነገር መጠናቀቁን ያሳያል፡፡

ምሳሌ፡- ራህመትና ዳንኤል ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው፡፡

<u>ለ. ጥያቄ ምልክት (?)</u>፡- ይህ ስርዓተ ነጥብ ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገርን ለመመስረት ይጠቅማል፡፡

ምሳሌ፡- እድሜሽ ስንት ነው?

፫. የሚከተሉትን ትግበራዎች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ጽሑፍ ላይ ተመስርታችሁ በተግባር አከናውኑ፡፡

ሀ. መምህራችሁ በሰሌዳው ላይ የሚጽፉላችሁን ፅሑፍ በጥንድ ሆናችሁ በጥሞና ደጋግማችሁ አንብቡ።

ለ. አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት የሌለበትን ጽሑፍ ስታነቡ በንበታችሁ ላይ ምን ለውጥ እንዳስከተለ ተወያዩበት።

፬. በዓርፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብ በመጠቀም የህይወት ታሪካችሁን ፃፉ።

ምሳሌ፡- ስሜ አስቴር ይባላል።

የተወለድኩት አዲስ አበባ ነው።

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. የሚከተሉትን ውስብስብ ፊደላት በሚገባ በማንበብ የተለያዩ ቃላትን መስርቱ።

| ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት |
|---|---|
| ምሳሌ:-ኋ | ጣኋት፣ በኋት... |
| 1. ኳ | |
| 2. ኂ | |
| 3. ኗ | |

፪. በሚከተሉት ሞክሼ ፊደላት ቃላት መስርቱ።

1. አ ፣ ዐ ________፣ ________
2. ጸ ፣ ፀ ________፣ ________

፫. የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት ስማቸውን ፃፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| 1 | 2 | 3 | 4 |

፬. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት የራሳችሁን የህይወት ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

### ራስን መግለፅ



- ስሜ፡- ሐያት ኢብራሒም እባላለሁ፡፡
- አባቴ፡- ኢብራሂም መሀመድ ይባላል፡፡
- እናቴ፡- ሰዓዳ ሁሴን ትባላለች፡፡
- ዕድሜዬ፡- ስምንት ነው፡፡
- ክፍሌ፡- ሁለተኛ “ለ” ነው፡፡
- ትምህርት ቤቴ፡- አፍላገ ግዮን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ይባላል፡፡
- የምኖረው፡- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 07 ነው፡፡
- ለወደፊት፡- መምህር መሆን እፈልጋለሁ፡፡
- የምወደው፡- መጽሐፍ ማንበብና ሽርሽር መሄድ ነው፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት
## ወቅቶች


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የአዳመጣችሁትን ፅሁፍ ዋና ዋና ሐሳብ በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በቃላችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ከ "ወቅቶች" ጋር ለተገናኙ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ድምፆችን ታጣምራላችሁ፣ ትነጥላችሁ፡፡
- ባለ አራት ፊደል ቃላትን ትፅፋላችሁ፡፡
- አራት ነጥብን በፅሁፍ ውስጥ ታስገባላችሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ኢትዮጵያና ወቅቶቿ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች የምታስታውሷቸውን የኢትዮጵያ ወቅቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስዕሉን አይታችሁ የምታዳምጡት ምንባብ ስለ ምን እንደሚያነሳ ገምቱ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ምላሽ ስጡ፡፡**

1.የአዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡

2.አሁን በሃገራችን ኢትዮጵያ ያለንበት ወቅት ማን ይባላል?

፪. የአዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የኢትዮጵያ ወራት አስር ናቸው፡፡
2. የህዳር ወር በመኸር ወቅት ውስጥ ይካተታል፡፡
3. ዝናብ የሚበዛበት ወቅት በልግ ይባላል፡፡

ቃላት

፩. በ"ሀ" ስር ያሉትን ወቅቶች ከ"ለ" ስር ካሉት ወራት ጋር አዛምዱ፡፡


| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|
| 1. መኸር | | ሀ. ታህሳስ |
| 2. በጋ | | ለ. ጥቅምት |
| 3. በልግ | | ሐ. ሐምሌ |

፪. ከአመቱ ወራት መካከል ባለ አራት ፊደል የሆኑትን በቻርቱ ላይ አሟሉ፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

፫. በምሳሌው መሰረት የጎደሉትን የሳምንቱ ቀናት ሞልታችሁ አንብቡ፡፡




## ንባብ



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የመስከረም ወር ሲመጣ ምን ምን በዓላት ትዝ ይሏችኋል?
2. ስዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ፡፡

## አበባ አየሁሽ

ሜዳና ተራራው በለምለም ሳርና አበባ አጊጧል፡፡ የጠዋቷ ፀሐይ ፍንትው ብላ ቀኑን አድምቃዋለች፡፡ የእነበፀሎት ሰፈር ልጆች በጋራ ተሰብስበው ፀጉራቸውን ተሰርተው ሐበሻ ቀሚሳቸውን ለብሰው ለመጨፈር ተዘጋጅተዋል፡፡ ሔለን ከበሮ ይዛለች፡፡ በፀሎትና ቡጡ ደግሞ አደይ አበባና ሳር ይዘዋል፡፡ ልጆቹም ወደ አቶ ይታገሱ ቤት በር ጠጋ ብለው በጭብጨባ የአበባ አየሁሽ ጭፈራን ጀመሩት፡፡ ቡጡ ፈጠን ብላ "አበባ አየሁሽ" ስትል ሁሉም በጋራ "ለምለም" በማለት ተቀበሏት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቡጡ | ባልንጀሮቼ | ልጆቹ | "ለምለም" |
| | ግቡ በተራ | | ለምለም |
| | እንጨት ሰብሬ | | ለምለም |
| | ቤት እስክሰራ | | ለምለም |
| | እንኳን ቤትና | | ለምለም |
| | የለኝም አጥር | | ለምለም |
| | እደጅ አድራለሁ | | ለምለም |
| | ኮከብ ስቆጥር | | ለምለም |
| | ኮከብ ቆጥሬ | | ለምለም |
| | ስገባ እቤቴ | | ለምለም |

## ምዕራፍ ሁለት

| | |
|---|---|
| ትቆጣኛለች | ለምለም |
| የእኔዋ እሜቴ | ለምለም |

አደይ የብር ሙዳይ ኮለል በይ (2 ጊዜ) እንዳለች አቶ ይታገሱ ከባለቤታቸው ወ/ሮ ውብዓለም ጋር በጋራ ወጥተው ለልጆቹ ዳቦ በመስጠት መረቋቸው፡፡ ልጆቹም፡-

ከብረው ይቆዩ ከብረው፣
በአመት አንድ ልጅ ወልደው፣
ሰላሳ ጥጃ አስረው፣
ከብረው ይቆዩ ከብረው፡፡

ብለው በጋራ መርቀው ወደ ቀጣዩ ቤት አመሩ፡፡

### አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሑፍ መልሱ፡፡

1. አበባ አየሁሽ የሚጨፈረው በየትኛው ወር ነው?
2. አበባ አየሁሽ የሚጨፍሩት እነማን ናቸው?
3. የምንባቡን ዋና ሐሳብ በቃል ተናገሩ፡፡

፪. በምንባቡ ውስጥ ያለው የበዓል መዝሙር በክፍላችሁ ከሚገኙ ጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በመለማመድ መምህራችሁ በሚያዟችሁ መንገድ በተግባር አሳዩ፡

### ☞ መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉት ቃላት በሚገባ በማንበብ በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ሆሄያት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ጳጉሜ = ጳ-ጉ-ሜ

ሀ. ሰኔ፡-________________ መ. ሐምሌ፡-________________

ለ. ጥር፡-________________ ሠ. ነሐሴ፡-________________

ሐ. ህዳር፡-________________

፪. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ጫማ + ዎች = ጫማዎች

| ቃላት | | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|---|
| 1. በሬ | | |
| 2. ሱሪ | | |
| 3. አበባ | ዎች | |
| 4. ኮፍያ | | |
| 5. ሜዳ | | |

፫. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማጣመር የተለያዩ ቃላትን መስርቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰ | ጠ | ቀ | 1. ቀጠረ | 6. |
| ት | ረ | መ | 2. | 7. |
| ለ | በ | ደ | 3. | 8. |
| ተ | ሸ | ከ | 4. | 9. |
| አ | ዘ | ጀ | 5. | 10. |

## ⊶ ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያ ድምፆች በሌላ ድምፆች ተክታችሁ ፃፉ፡፡ ከዚያም የሁለቱን ቃላት ልዩነት በቃል ግለፁ፡፡

ምሳሌ፡- ሰኔ = የኔ፣ ቅኔ …

1. ጥር = ____________  4. በጋ = ____________
2. ቀን = ____________  5. በላ = ____________
3. ሰኞ = ____________

## አቀላጥፎ ማንበብ

የሚከተለውን ምንባብ በመደጋገም ትክክለኛውን የአነባበብ ሥርዓት ተከትላችሁ አንብቡ፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

## አካባቢያችንን እንጠብቅ

የምንኖርበትና የምንማርበት አካባቢ ሁልጊዜም ንፁህ መሆን አለበት፡፡ አካባቢያችን ንፁህ ከሆነ በሽታ አይዘንም፡፡ ለዓይናችንም የሚያስደስት ይሆናል፡፡ ለዓይናችን ደስ የሚል ከሆነ ደግሞ ደስተኞች እንሆናለን፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ እያንዳንዳችን አካባቢያችንን ማፅዳት፤ ልዩ ልዩ እፅዋትንና አበባዎችን መትከል አለብን፡፡ ይህን ስናደርግ የመሬታችን አፈርም አይሸረሸርም፡፡ ስለዚህ አንድ ተክል ስንቆርጥ በምትኩ ሌላ ችግኝ መትከል ይኖርብናል፡፡ ይህንን ካደረግን ሁልጊዜ ጤናማና ደስተኛ እንሆናለን፡፡ አካባቢያችንም ውብ ይሆናል፡፡

(አላምረው 2002፣ 91 ለማስተማሪያነት እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

## ✍ ጽሕፈት

፩. ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በሚገባ በማዳመጥ:-

ሀ. ቃላቱን በደብተራችሁ ፅፋችሁ አንብቧቸው፡፡

ለ. የፃፋችኋቸውን ቃላት የመጀመሪያውን ፊደል አጥፍታችሁ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ሐ. ባጠፋችኋቸው ፊደላት ምትክ ሌላ አንድ ፊደል በመተካት በምሳሌው መሰረት ቃሉን ሌላ ፍቺ እንዲኖረው አድርጉ፡፡

ምሳሌ:- ህዳር - ("ህ" ፊደል ስትወገድ) ዳር - ("አ" ፊደል በ ህ ስትተካ (ስትጨመር) አዳር ይሆናል፡፡

<u>ህዳር</u>፣ <u>ዳር</u>፣ <u>አዳር</u>

1. ______________፣ ______________፣ ______________
2. ______________፣ ______________፣ ______________
3. ______________፣ ______________፣ ______________
4. ______________፣ ______________፣ ______________
5. ______________፣ ______________፣ ______________

፪. ተማሪዎች በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ቃላት በዓ.ነገር ውስጥ በማስገባት የተለያየ ፍቺ እንዲሰጡ አድርጉ፡፡

ምሳሌ፡- በላ ሀ. ሰኢድ ምሳው በላ፡፡ (ተመገበ)
ለ. አደናይ የውድድሩን ዋንጫ በላ፡፡(አሸነፈ)

1. ሔደ
2. ዓይኖች
3. ውኃ
4. ጠላ
5. ተሾመ

፫. በሚከተለው ፅሑፍ ውስጥ አራት ነጥብ (፡፡) በማካተት ፅሑፉን የተሟላ አድርጉ፡፡

## በጋ እና ክረምት

በጋ የፀሐይ ወቅት ነው ብዙ ጊዜ ዝናብ አይጥልም ወንዞች በጣም ይቀንሳሉ እህሎች ወደ ጎተራ ይከተታሉ በጋ ለጉዞ በጣም አመቺ ነው ለከብቶች መጠጥና የግጦሽ ሳር ችግር ይኖራል

ክረምት የዝናብ ወቅት ነው በዚህ ወቅት ብዙ ተክሎች ይበቅላሉ ወንዞች ብዙ ውኃ ይኖራቸዋል እንስሳት ውኃ እንደልባቸው ያገኛሉ ብዙ እህሎች ይበቅላሉ ገበሬዎችም በቂ ዝናብ ካገኙ ጥሩ ምርት ያገኛሉ

# ምዕራፍ ሁለት

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. ከዚህ በታች የቀረበውን ፅሑፍ በትኩረት አንብቡ፤ ከዚያም ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ ስጡ።

### እስኪ እወቁኝ

በኢትዮጵያ ብቻ የምገኝ ብርቅዬ ወር ነኝ። አምስት ወይም ስድስት ቀናት አሉኝ። ከአራት ዓመት አንዴ ስድስት ቀን እሆናለሁ። በሌሎች ዓመታት ግን አምስት ቀን ነኝ። ከነሐሴ ወደመስከረም ድልድይ ሆኜ አሻግራለሁ። የአዲስ ዓመት ብስራት ተስፋን እሰንቃለሁ።

1. እኔ ማን ነኝ?
2. የዓመቱ ስንተኛ ወር ነኝ?
3. እኔ ከየትኛው ወር በኋላ እገኛለሁ?
4. ለምንድን ነው ብርቅዬ የተባልኩት?
5. በየትኛው ወቅት እገኛለሁ?

፪. የሚከተሉትን ፊደላት በማገጣጠም ቃላት መስርቱ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | ጓ | እ | በ | አ | ተ | ና |
| ድ | ን | ኛ | ጫ | ች | ወ | ት |

1. ተናደደ
2. ______
3. ______
4. ______
5. ______
6. ______

፫. በ"ሀ" ስር ያሉትን ቃላት በ"ለ" ስር ካሉት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ብርድ | ሀ. እህል መክተቻ |
| 2. ንጹህ | ለ. ምርት |
| 3. ጎተራ | ሐ. ያማረ |
| 4. ሰብል | መ. ጽዱ |
| 5. ውብ | ሠ. ቅዝቃዜ |

# ምዕራፍ ሶስት
## ታሪኮች


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የአዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ለይታችሁ ቃላዊ ዘገባ ታቀርባላችሁ::
- ካነበባችሁት ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳብ ትፅፋላችሁ::
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ትጠቀማላችሁ::
- ባለአራት ፊደል ቃላትን ትመሰርታላችሁ::
- ቃል አጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን በጽሑፍ ውስጥ ትጠቀማላችሁ::

## አውራዶሮ እና ቀበሮ

### ማዳመጥ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ከላይ ያለውን ስዕል በመመልከት የምታዳምጡት ምንባብ ስለ ምን እንደሚያነሳ ገምቱ፡፡
2. ተረት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

### አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. በታሪኩ ውስጥ የተራበው ማን ነው?

ለ. አውራ ዶሮው በቀበሮ የተያዘው እንዴት ነው?

ሐ. እናንተ በዶሮው ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

፪. ያዳመጣችሁትን ምንባብ በማስታወስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፫. የምታውቁትን አንድ ታሪክ ወይም ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ስርዓቱን ጠብቃችሁ በቃል ተርኩ፡፡

## ⊶ ቃላት

፩. በምንባቡ መሰረት በ"ሀ" ስር ላሉት ቃላት ከ"ለ" ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|
| 1. ተጣደፈ | | ሀ. ዘዴ |
| 2. ፈረጠጠ | | ለ. ደን |
| 3. ጫካ | | ሐ. ሮጠ |
| 4. ድርጊት | | መ. ተግባር |
| 5. ብልሃት | | ሠ. ቸኮለ |

## ☞ መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በማጣመር ፃፉ።

| ምሳሌ፡- ከ - መንደር = ከመንደር<br>ዶሮ - ው = ዶሮው | |
|---|---|
| 1. ጀመረ - ች | |
| 2. አፉ - ን | |
| 3. ቀበሮ - ው | |
| 4. ወደ - ጫካ | |
| 5. ለ - መናገር | |


፪. በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በብዙ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ነጠላ ቁጥር በመቀየር ፃፉ።

ምሳሌ፡- ተማሪዎች = ተማሪ ደብተሮች = ደብተር

1. ቅርሶች = ____________
2. መጽሃፎች = ____________
3. ገበሬዎች = ____________
4. በሬዎች = ____________
5. ጫማዎች = ____________

## ንባብ







### ቅድመ ንባብ

1. የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማን ናት?
2. ቅርሶችን ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ ምን ምን ቅርሶችን ጎብኝታችኋል፡፡

## አዲስ አበባ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት፡፡ የተመሰረተችው 1879 ዓ.ም. በዳግማዊ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ነው፡፡ ይህች ከተማ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ በሰላምና በፍቅር ይኖሩባታል፡፡ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫም ናት፡፡ በርካታ የሚጎበኙ ቅርሶች አሏት፡፡

---

ተማሪዎች አዲስ አበባ ምን ምን ቅርሶች አሏት ብላችሁ ታስባላችሁ?

---

በውስጧ ከሚገኙ ቅርሶች መካከል የቀደምት ዘመናት የኪነ-ህንጻ አሰራሮች፣ ቤተ-መንግስቶች፣ ሙዚየሞች (እንጦጦ ሙዚየም፣ ብሄራዊ ሙዚየም፣ አራት ኪሎ ሙዚየም፣ ወዘተ.) ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም የአርበኞች ሀውልት፣ የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት፣ የካቲት 12 ሀውልት፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ በተጨማሪም የጎብኝዎችን ቀልብ የሚስቡ እንጦጦና አንድነት ፓርክ ይገኙባታል፡፡ ሁሉንም ስናያቸው የኢትዮጵያን ባህል፣ ሐይማኖት፣ ታሪክና የየዘመኑ ክስተቶችን የሚያወሱ ናቸው፡፡ እነዚህንም የተለያዩ ቱሪስቶች መጥተው ሲጎበኙ የሚያርፉባቸው ዘመናዊ ሆቴሎች የራሳቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

### ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. አዲስ አበባን የመሰረቷት እነማን ናቸው?
2. በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅርሶች ምንምን ናቸው?
3. አዲስ አበባ ከተመሰረተች ስንት አመት ሆናት?
4. በምንባቡ ውስጥ ስንት አራት ነጥቦች ይገኛሉ?

### ፪. "አዲስ አበባ" ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት መስመር በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

## ቃላት

ከምንባብ ለወጡ ቃላት በክቡ ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

1. በርካታ = ____________
2. ፍቅር = ____________
3. ሰላም = ____________
4. ከተማ = ____________
5. ድሮ = ____________


ገጠር
ጥላቻ ልዩነት
ጦርነት ጥቂት
ዘንድሮ

## አቀላጥፎ ማንበብ

የሚከተለውን ምንባብ በመደጋገም ትክክለኛውን የአነባበብ ሥርዓት ተከትላችሁ አንብቡ።

### እናስተዋውቃችሁ!

ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረስላሴ ቢልልኝ ይባላሉ። አርበኛና መምህር ናቸው። አባታቸው መምህር ገብረስላሴ ቢልልኝ ይባላሉ። እናታቸው ደግሞ ስዕለሚካኤል ወልደአብ ናቸው። የተወለዱት ታህሳስ 24 ቀን 1894 ዓመተ ምህረት በቡልጋ ክፍለ ሀገር ነው። ከእጽዋት ቀለም ያዘጋጃሉ። ብራና ፍቀው በመቃ ብዕር ይጽፋሉ። ግንቦት 26 ቀን 1992 ዓመተ ምህረት በ97 ዓመታቸው አርፈዋል። ነገር ግን ሥራቸው ትውልድ እስካለ ድረስ ይቀጥላል።



እኚህ አባት አሁን እናንተ ከቅድመ መጀመሪያ (ኬጂ) እስከ አሁን እየተማራችሁበት ያለውን "የፊደል ገበታ" የጻፉ አባት ናቸው:: የፊደል ገበታን በሶስት ረድፍ በመክፈል (በሀ..ሁ..ሂ፤ መልዕክተ ዮሀንስ፤ አ..ቡ..ጊ...) በእጃቸው በመጻፍና በማሳተም ለኢትዮጵያ ህጻናት በሙሉ እንዲዳረስ አድርገዋል:: ስለዚህ ሁልጊዜ ልናስታውሳቸውና ልናመሰግናቸው ይገባል:: ልጆች እናንተም እንደተስፋ ገብረስላሴ ለወገንና ለሀገር የሚተርፍ ሥራ ለመስራት ጎበዝ ተማሪ መሆን አለባችሁ::

## ✍ ጽሕፈት

፩. ከላይ "እናስተዋውቃችሁ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ባለ አራት ፊደል ቃላትን ለይታችሁ ፃፉ::

ምሳሌ:- ህጻናት

፪. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉትን ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ::

ምሳሌ:- አርፈዋል = ሞተዋል

ሀ. ብዕር = __________ መ. ወገን = __________

ለ. ፊደል = __________ ሠ. ጎበዝ = __________

ሐ. ህጻናት = __________

# ምዕራፍ ሶስት

፫. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማጣመር ቃላት መስርቱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስ | ተ | ራ | ት |
| ታ | ር | ክ | ፋ |
| ቅ | ረ | በ | ሪ |

ምሳሌ፡- ታሪክ

፬. በትዕዛዝ ሶስት ላይ በመሰረታችኋቸው ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ታሪክ = 1. ዓባይ የዘመኑ ታሪክ ነው፡፡

2. ኤፍራታ የህይወት ታሪክ ጻፈች፡፡

፭.ከተለያዩ ሰዎች የሰማችኋቸው ተረቶች ወይም ከመፅሃፍት ካነበባችኋቸው ታሪኮች መካከል አንዱን በመምረጥ ስርዓቱን ጠብቃችሁ በአጭሩ ፃፉ፡፡

**ቃለ አጋኖ (!)**

ቃለ አጋኖ የመገረምን፣ የመደሰትን፣ የመከፋትን፣ የመደሰትን... ስሜት የምንገልጽበት ሥርዓተ ነጥብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ልብሱ እንዴት ያምራል!

አቤት ውሸት!

፮. አራት ነጥብን (፡፡)፣ እና ጥያቄ ምልክትን (?) በመጠቀም

አራት ዓረፍተ ነገሮችን ሥሩ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በማጣመር ባለ 2፣ ባለ 3፣ እና ባለ 4 ፊደል ቃላትን መስርቱ፡፡

| የተዘበራረቁ ፊደላት | ባለ 2 ፊደል ቃላት | ባለ 3 ፊደል ቃላት | ባለ 4 ፊደል ቃላት |
|---|---|---|---|
| ደ፣ ተ፣ ጠ፣ ር<br>ች፣ ፊ፣ ብ፣ ስ<br>ጣ፣ ረ፣ አ፣ ሰ፣ ን፣<br>ራ፣ በ፣ ጌ፣ ወ | ንብ | ባለጌ | አበጠረ |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

፪. የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥቦች በቡድን ሆናችሁ ስማቸውን እና አገልግሎታቸውን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡ ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ስርዓተ ነጥቦች | መጠሪያ | አገልግሎት |
|---|---|---|---|
| 1. | ፡፡ | | |
| 2. | ? | | |
| 3. | ! | | |

አማርኛ

፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት
## የአትክልት ቦታ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ:-

- የአዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሀሳብ ትለያላችሁ።
- ካነበባችሁት ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳብ ትፅፋላችሁ።
- ቃል አጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ትለያላችሁ።

## ማዳመጥ

### የማርታ ማስታወሻ

## ማዳመጥ





## ቅድመ ማዳመጥ

1. በምትኖሩበት አካባቢ መናፈሻዎች (የአትክልት ቦታዎች) አሉ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ ምን ምን የአትክልት ቦታዎች አሉ?
2. ርዕሱን እና ምሥሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሆነ ግምታችሁን ተናገሩ::
3. የአትክልት ስፍራ መኖር ምን ጥቅም አለው?

## ምዕራፍ አራት

### አዳምጦ መናገር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት  በቃል መልሱ።

ሀ. ማርታ ለምን ተሸለመች?

ለ. ማርታ ከአባቷ ጋር ለመዝናናት የሄደችበት ስፍራ ምን ይባላል? የትስ ይገኛል?

ሐ. እነማርታ የጎበኙትን መናፈሻ ከሚላት ለማየት የጓጓችው ለምንድን ነው?

መ. የምንባቡ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

### ቃላት

በ"ሀ" ስር ያሉትን ስዕሎች በ"ለ" ስር ካሉት መግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ።

| ስዕሎች | መልስ | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ.ዘር መዝራት |
| 2.  | | ለ.በጋራ መስራት |
| 3.  | | ሐ.መቆፈር |
| 4.  | | መ.አበባ መትከል |
| 5.  | | ሠ.ውሃ ማጠጣት |

## መነጠልና ማጣመር

### ፩. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት፡-

ሀ. በሚገባ በማዳመጥ ቃላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ፡፡
ለ. የፃፋችኋቸውን ቃላት ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላት መስርቱ፡፡
ሐ. ቦታ በመቀያየር የፃፋችኋቸውን ቃላት ላይ ሌላ ፊደል በመጨመር ቃላቱ የተለየ ፍቺ እንዲሰጥ አድርጉ፡፡

### ፪. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ሆሄያትን በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ፡፡

| የተነጣጠሉ ቃላት | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|
| 1. የ - ህፃናት | የህፃናት |
| 2. አንድ - ነት | አንድነት |
| 3. የሚ - ከበር - በት | የሚከበርበት |
| 4. እንዲ - ያስቡ - ት | እንዲያስቡት |
| 5. ሲ - መለስ | ሲመለስ |
| 6. የ - አካባቢ - ው | የአካባቢው |

## ፫. በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በብዙ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ነጠላ ቁጥር በመቀየር ፃፉ።

ምሳሌ፡- ሰራተኞች = ሰራተኛ

ካልሲዎች = ካልሲ

1. ቤቶች = ______________
2. ቢራቢሮዎች = __________
3. እርሳሶች = _____________
4. መኪናዎች = ___________
5. መኪናዎች = ___________
6. ዶማዎች = _____________

## ንባብ







ቅድመ ንባብ

1. አንድን ግቢ ሊያስውቡ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ተናገሩ?
2. ከስዕሉ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ?

## "አበባማው ግቢ"

የህፃናት ቀን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ ሰኔ 9 ቀን ይከበራል፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ነው፡፡ የሚከበርበትም ምክንያት የህፃናትን ደህንነት፣ ጥበቃና መልካም አስተዳደግ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ይህን በማሰብ መምህርት ትህትና እና መምህር ጀማል ከሰኔ 5 እስከ 9 ድረስ አበቦችና የተለያዩ ችግኞች በመትከል፤ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን በማቅረብ እንዲከበር ያደርጋሉ፡፡

ተማሪዎች የህፃናት ቀን የሚከበርበትም ምክንያት ምንድን ነው?

ከመምህርት ትህትና ተማሪዎች አንዱ ኬብሮን ነው፡፡ ኬብሮንም በህፃናት ቀን አከባበር ላይ የተከላቸውን አበቦች ሲያይ በጣም ተደሰተ፡፡ በክረምት ወቅትም አበቦችንና የተለያዩ ተክሎችን መትከልና መንከባከብ እንዳለበት አሰበ፡፡ ሀሳቡንም በተግባር ላይ አዋለው፡፡ እናቱና አባቱም በሚሰራው ስራ ደስተኛ በመሆናቸው ያግዙታል፡፡ በግቢው በርካታ አበባዎች በመተከላቸውም የእነኬብሮን ግቢ "አበባማው ግቢ" በሚል ስም መጠራት ጀመረ፡፡ ሰዎችም የእነኬብሮንን ግቢ ለማየት ሁሌ ይጓጓሉ፡፡ የኬብሮን እናትና አባትም የሰፈሩ ሰዎችን አድናቆትና ልዩ ስሜት በማየታቸው ተደሰቱ፡፡ ከአካባቢ ነዋሪዎችም ጋር መመካከር፣ በጋራ አካባቢያቸውን ማፅዳትና አበባ መትከል ጀመሩ፡፡ አካባቢያቸውም እጅግ የሚያምር፣ ፅዱና ማራኪ ሆነ፡፡

## አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ።**

1. ተማሪ ኬብሮን ግቢውን በአትክልት እንዲያስውብ ያነሳሳው ምክንያት ምንድን ነው?
2. እናንተ የምትኖሩበትን ግቢና አካባቢ ለማስዋብ ምን ምን መንገዶችን ትጠቀማላችሁ?
3. የህፃናት ቀን በስንት ዓመተ ምህረት መከበር ጀመረ?

**፪. "አበባማው ግቢ" ከሚለው ምንባብ ምን እንደተማራችሁ በሶስት ዓረፍተ ነገር ሀሳባችሁን ግለፁ**

## ⊶ ቃላት

**፩. በሚከተሉት ፊደላት የሚመሰረቱ ቃላትን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ በፊደላቱ ጎን ፃፉ።**


1.ተ = ተክል፣ ተማሪዎች

2.መ = ________________

3.ሐ = ________________

4.አ = ________________


5.ዕ = ________________



፱. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታው ላይ ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |
| 1. | 2. | 3. | 4. | 5. |

፲. የሚከተሉትን ፊደላት በመገጣጠም ባለአምስት ፊደል ቃላት መስርቱ።




1. ______________
2. ______________
3. ______________
4. ______________
5. ______________

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩. ከላይ "አበባማው ግቢ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ እየተነሳችሁ አንብቡላቸው።

፪. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ስርዓተ- ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንብቡ።

1. በአሁን ሰዓት የኮሮና ስርጭት ምን ያህል ነው?
2. ችግኝ መትከል የአካባቢን የአየር ንብረት ያስተካክላል።
3. ሁለተኛ ይህን መጥፎ ድርጊት ስትሰራ እንዳላይህ!
4. ሀገሬ ለእኔ ሁሉ ነገሬ ናት።
5. የአባይ ግድብ በመገንባቱ እንኳን ደስ አላችሁ!
6. የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናችሁ?

## ✍ጽሕፈት

፩. በምሳሌው መሰረት በሚከተሉትን ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ሳር = ልጁ ሳር ተከለ።

1. አካፋ
2. አበባ
3. መኮትኮቻ
4. ውሃ
5. አፈር

፬. ቃለ አጋኖ ስርዓተ ነጥብን በመጠቀም ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

፫. የሚከተለውን ጽሁፍ በቡድን ሆናችሁ በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ ሥር ያሉ ተግባራት ስሩ፡፡

## የማዕዶት አጎት

የማዕዶት አጎት መክብብ ይበልጣል ይባላል፡፡ መክብብ ይበልጣል የማዕዶት አባት ወንድም ነው፡፡ እድሜው 35 ሲሆን ስራው አትክልተኛ ነው፡፡ ሙያውን የሚያከብርና ጠንክሮ የሚሰራ ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡ በዚህ ስራው በጉለሌ የእፅዋት ማዕከል ውስጥ ያሉትን እፅዋት በአግባቡ በመንከባከቡ ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡ ለወደፊት የራሱ የእፅዋት ማዕከል ከፍቶ መስራት ይፈልጋል፡፡

ሀ. ጽሁፉ እንዴት እንደተፃፈ አስተውሉ፡፡

ለ. ከቤተሰቦቻችሁ ወይም ከምታውቋቸው ሰዎች አንዳቸውን በመምረጥ ባነበባችሁት ጽሁፍ መሰረት የህይወት ታሪካቸውን በየግል ፃፉ፡፡

ሐ. በየግል የፃፋችሁትን የህይወት ታሪክ ለቡድን አባላቶቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

መ. ከፃፋችኋቸው የህይወት ታሪኮች አንዱን በመምረጥ በጋራ አዳብራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፬. “የማዕዶት አጎት” የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- አጎት= የአባት ወንድም


ሀ. ታታሪ = ______________ መ. ለወደፊት = ______________

ለ. ማዕከል = ______________ ሠ. ሙያውን = ______________

ሐ. ጠንክሮ = ______________

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር ፃፉ።




| ቃላት | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|
| ምክር | ምክር ቤት |
| ትምህርት | |
| ፍርድ | |
| ሻይ | |
| ጎጆ | |
| መስሪያ | |

፪. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በማጣመር ባለ 3፣ ባለ 4 እና ባለ 5 ፊደል ቃላትን መስርቱ።

| የተዘበራረቁ ቃላት | ባለ 3 ፊደል ቃላት | ባለ 4 ፊደል ቃላት | ባለ 5 ፊደል ቃላት |
|---|---|---|---|
| ኢ፣ቤ፣ብ፣ን፣ጎ | | | |
| በ፣የ፣ር፣ጠ፣ | | | |
| ዥ፣ት፣ሪ፣አ፣ተ | | | |
| ሪ፣ም፣ወ፣ክ፣ያ | | | |
| ል፣ማ፣ጵ፣ህ፣ስ | | | |

፫. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታዎች ላይ ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |
| 1. | 2. | 3. | 4. | 5. |

# ምዕራፍ አምስት
## የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ታወጣላችሁ፡፡
- ቃለ አጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ትለያላችሁ፡፡
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ታስገባላችሁ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማዳመጥ

## የጤና ቁልፍ




### ቅድመ-ማዳመጥ

1. ወደትምህርት ቤት ከመምጣታችሁ በፊት ምን ምን ተግባራት ታከናውናላችሁ?
2. ስዕሉን በመመልከት ስለምን እንደምታዳምጡ ገምቱ?

### አዳምጦ መናገር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ፀጉር ማበጠር ከአካባቢ ንፅህና ይመደባል፡፡
2. ልጆቹ ተረት ለማደመጥ የሄዱት ሰዓት አክብረው ነው፡፡
3. የግል ንፅህናን ብቻ መጠበቅ ለጤና ጠቀሚ ነው፡፡
4. መጥረግ፣ መትከልና መንከባከብ የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ተግባራት ናቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

፩. በ "ሀ" ስር ላሉትን ቃላት ከ "ለ" ስር ተመሳሳያቸውን ፈልጉ፡፡

| ምሳሌ | "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|---|
| | ተጣደፈ | ረ | ሀ. የራስ |
| 1. | ተወ | | ለ. በህብረት |
| 2. | አየ | | ሐ. ይጠቅማል |
| 3. | የግል | | መ. ሁልጊዜ |
| 4. | ዘወትር | | ሠ. ተመለከተ |
| 5. | ያስፈልጋል | | ረ. ተቻኮለ |
| 6. | በጋራ | | ሰ. አቆመ |

፬. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን በመጠቀም ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- በግላችን = በግ፣ በላ

1. ጥርሳችን = ____________ 4. ማበጠር = ______________

2. ያስፈልጋል = __________ 5. ማስጠበቅ = ___________

3. መምጣት = _____________

ማጣመርና መነጠል

፩. የሚከተሉትን ተነጣጥለው የተቀመጡትን ቃላት አጣምራችሁ አንብቡና ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የ - አካባቢ - ያችን - ን = የአካባቢያችንን

1. ወደ - ቤታ - ቸው = _____________________

2. እናንተ - ም = ___________________________

3. በ - ህይወት = ___________________________

4. ሊያ - ወሩ - ት = _______________________

5. ፀጉራ - ችሁ - ን = ______________________

፪. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉት ቃላት መነሻ ላይ “አል-” በመጨረሻ ላይ “-ም” በመጨመር ቃላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡- ሰራ = አል- ሰራ -ም = አልሰራም

1. ታጠበ = አል- _____________ -ም = _______________

2. ፋቀች = አል- _____________ -ም = _______________

3. ፀዳ = አል- _____________ -ም = _______________

4. ቆረጠ = አል- _____________ -ም = _______________

5. ሰራች = አል- _____________ -ም = _______________

# ምዕራፍ አምስት



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች የአካባቢን ንፅህና አለመጠበቅ ጉዳት ያስከትላል? አዎ ካላችሁ ጉዳቶቹን ዘርዝሩ፡፡
2. የግልና አካባቢ ንፅህናን አንድነትና ልዩነት ተናገሩ፡፡

### "ታሞ ከመማቀቅ..."

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ ነጋዴዎቹ የተለያዩ አትክልት፣ ፍራፍሬና ጥራጥሬ እንዲሁም አልባሳትን በመሸጥ ይተዳደራሉ፡፡ ሁሉም ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩት ከንግድ በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ የአካባቢው ሰዎችም የተለያዩ ነገሮችን ከእነርሱ እየገዙ ይመገባሉ፤ ይለብሳሉ፡፡ ነጋዴዎቹ በንግድ ቦታቸው የተለያዩ ማስታወቂያዎችን ለጥፈዋል፡፡ "ዱቤ ነገ እንጂ ዛሬ የለም!"፤ "የአፍ ጭንብል (ማስክ) ካላደረጉ አናስተናግድም!"፤ "ካለ ስራ መቆም ክልክል ነው!"...፡፡ ይሁንና ለንፅህና ብዙ ትኩረት ስለማይሰጡ የተለያዩ ቆሻሻዎችን በየቦታው ይጥላሉ፡

| |
|---|
| ተማሪዎች! ነጋዴዎቹ ለአካባቢ ንፅህና ትኩረት ባለመስጠታቸው ምን የሚከሰት ይመስላችኋል? |

በቆሻሻው መብዛት ምክንያት አካባቢው በመጥፎ ጠረን ታወከ፡ ፡ነዋሪዎቹም የቆሻሻው ሽታ ስለረበሻቸው ራቅ ወዳለ ቦታ እየሔዱ መገበያየት ጀመሩ፡፡ ሩቅ ቦታ ሔደው መገበያየታቸው ለተለያዩ እንግልት ዳረጋቸው፡፡ በዚህም በጣም መማረር ጀመሩ፡ ፡ ነጋዴዎቹም ሰርቶ ማገኘትን ብቻ በማሰብ ደፋ ቀና ሲሉ ተራ በተራ ታመው ተኙ፡፡ ቤተሰቦቻቸውም እነርሱን በማስታመም ስለተወጠሩ የዕለት ጉርሻቸውን ማግኘት አቃታቸው፡፡ ነጋዴዎቹም

ሆኑ ነዋሪዎቹ በጣም ስለተቸገሩ በጋራ ሆነው መወያየት ጀመሩ፡ ፡ በውይይታቸውም አንድ የመፍትሔ ሐሳብ ላይ ደረሱ፡፡ "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" ነው፤ በማለት በጋራ ሆነው አካባቢያቸውን ለማፅዳትና ለመንከባከብ ተስማሙ፡፡ በቀጣዩ ቀን በጠዋት ተነስተው አካባቢያቸውን አፀዱ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ሁለም በደስታና በጤና መኖር ጀመሩ፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ አክብቡ፡፡

1. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሰው ሐሳብ ትኩረቱ _____ ላይ ነው?

   ሀ. የግል ንፅህና ለ. የአካባቢ ንፅህና ሐ. የቤት ንፅህና

2. በአንድ አካባቢ የሚኖሩት እነማን ናቸው?

   ሀ. ነዋሪዎቹ ለ. ነጋዴዎቹ ሐ. ሁለቱም

3. ነዋሪዎቹ ወደሌላ ቦታ ሔደው የተገበያዩት ለምንድን ነው?

   ሀ. እርስ በርስ በመጣላታቸው

   ለ. የአፍ ጭንብል (ማስክ) ባለማረጋቸው

   ሐ. አካባቢያቸው ስለቆሸሸና ስለሸተታቸው

4. ነዋሪዎቹ እና ነጋዴዎቹ ተወያይተው ምን ወሰኑ?

   ሀ. አካባቢቸውን ለቆ መሔድ

   ለ. በጋራ አካባቢን ማፅዳት

   ሐ. አለመገበያየት

፪. ምንባቡ የሚያስተላልፈውን ዋና መልዕክት በቡድን ሆናችሁ በመወያየት በሁለት ዓረፍተ ነገር ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩.ተማሪዎች “ታሞ ከመማቀቅ...” የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

፪.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክለኛ የአነባብ ስልት አንብቧቸው፡፡

ሀ. መንገድ ከማቋረጤ በፊት ግራና ቀኝ እመለከታለሁ፡፡

ለ. ቅዳሜና እሁድ ምን ትሰራላችሁ?

ሐ. እንኳን አደረሳችሁ!

## ቃላት

፩. በ “ሀ” ስር ላሉት ቃላት ከ “ለ” ስር ካሉት ቃላት ተቃራኒ ፈልጉላቸው፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ቅርብ | ሀ. ከፊት |
| 2. ከኋላ | ለ. ይበልጣል |
| 3. መጣ | ሐ. ወደደ |
| 4. ያንሳል | መ. ሔደ |
| 5. ጠላ | ሠ. ሩቅ |

፬. በ “ሀ” ስር ባሉት ቃላት የተመሰረቱትን ዓረፍተ ነገሮች ከ “ለ” ስር በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጤና ______ | ሀ. የአካባቢው ውበት ይማርካል። |
| 2. ንፅህና ______ | ለ. ቆሻሻ ለጤና ጠንቅ ነው። |
| 3. ውበት ______ | ሐ. አካባቢን ለማፅዳት ህብረት ያስፈልጋል። |
| 4. ቆሻሻ ______ | መ. ለሰው ልጅ ጤና አስፈላጊ ነው። |
| 5. ህብረት ______ | ሠ. የአካባቢያችን ንፅህና እንጠብቅ። |


፭. የሚከተሉትን ስዕሎች ከመግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ።


ማጠብ


መቦረሽ


ማበጠር


መጥረግ


መታጠብ


መቁረጥ

፬. የሚከተሉትን ፊደላት በመምረጥ በክፍት ቦታው ላይ በመሙላት ቃላቱን የተሟሉ አድርጓቸው።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ታ | ስ | ጉ | ፀ | ት | ሽ | ጠ | ጥ |

1. ብሩ____
2. ፀ___ር
3. ጥር___
4. መ__ጠብ
5. ፊ_____
6. ማበ___ሪያ
7. መ____ረግ

☞ማጣመርና መነጠል

በምሳሌው መሰረት በሚከተሉትን ቃላት ውስጥ ያሉ ሆህያትን በመነጣጠል አንብቡና በማጣመር ፃፉ።

ምሳሌ፡ የ - አፍሪካ = የአፍሪካ

ጊዜ - ያቸ - ው = ጊዜያቸው

1. ሸለመ - ች - ኝ = ________________

2. አረንጓዴ - ው = ________________

3. እየ- ተባለ = ________________

4. የተ - መሰረተ - ው = ________________

5. እንደ - ሚያምር = ________________

## ✍ ጽሕፈት

፩. በክቡ ውስጥ ያሉ ቃላትን በተስማሚው ክፍት ቦታ አስገብታችሁ ዓረፍተ ነገሩን የተሟላ አድርጉ፡፡

ንፅህና ተማሪዎች ቀን ግል ፀጉሩን

1. ____________ክፍላቸውን አፀዱ፡፡
2. የሱፍ ____________ አበጠረ፡፡
3. ተማሪዎች የፅዳት ____________ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
4. የግልና የአካባቢ ____________ መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡
5. ገላን መታጠብ የ____________ ንፅህና ነው፡፡

፪. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በማዳመጥ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

፫. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ላይ አራት ነጥብ (፡፡) በመጨመር ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ፡፡

1. ጤናማ ህፃናት በአዕምሮና በአካል ብቁ ናቸው
2. ጥርስን ዘወትር መቦረሽ ያስፈልጋል
3. የግል ንፅህናችንን ከጠበቅን ጤነኛ እንሆናለን
4. ንፁህ አካባቢ ለመዝናኛ ጥሩ ነው
5. የግል ንፅህናችንን በመጠበቅ ራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ እንከላከል

# ምዕራፍ ስድስት

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታዎች ላይ ፃፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  1. |  2. |  3. |   4. |  5. |
| | | | | |

፪. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በተስማሚ ክፍት ቦታዎች ውስጥ አሟሉ፡፡

| ሐይቆች | ላም | ሩጫ | ሱሪ | ሹካ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

1. ፓስታ በ ________ይበላል፡፡
2. ________ ወተት ትሰጣለች፡፡
3. ዳንኤል __________ ተገዛለት፡፡
4. ነገ የ ____________ ውድድር አለ፡፡
5. ኢትዮጵያ ብዙ ____________ አሏት፡፡

## ፫. በሚከተሉትን ቃላት የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሔደ፡- እስማኤል ምሳውን በልቶ ሔደ፡፡

ሊጥ፡- ባልዲው ውስጥ ሊጥ አለ፡፡

1. አፈር፡- ______________________________፡፡
2. ፈረስ፡- ______________________________፡፡
3. አረሰ፡- ______________________________፡፡
4. አጠናች፡- ______________________________፡፡
5. ድልድይ፡- ______________________________፡፡

አማርኛ
፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት
## ባህላዊ ሙዚቃ


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ፅሑፍን አዳምጣችሁ ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ::
- ከሚነበብ ጽሑፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ትሰጣላችሁ::
- የጥያቄ ምልክትንና ቃልአጋኖን ትጠቀማላችሁ::
- ቃላትን ከመነሻ ቅጥያቸው ጋር አጣምራችሁ ትጠራላችሁ::

## ማዳመጥ

**ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች**



### ቅድመ-ማዳመጥ

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ ምን ምን ታውቃላችሁ? ዘርዝሩ።
2. ባህላዊ ጭፈራ ማለት ምን ማለት ነው?

## አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት የሆኑትን ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ፡፡




1. ከበሮ የትንፋሽ ባህላዊ መሳሪያ ነው፡፡
2. ዋሽንት አምስት ክሮች አሉት፡፡
3. ከጅማት ክርና ከእንጨት የሚሰራው ክራር ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ በቡድን ሆናችሁ ለጥያቄዎቹ በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. ከምታውቁት ባህላዊ ጭፈራ (ውዝዋዜ) የአንዱን የአተገባበር ሂደት በማስታወሻ በመያዝ በቃል ተናገሩ፡፡
2. መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት ቡድን መስርታችሁ ስላዳመጣችሁት ምንባብና ስለተወያያችሁበት ባህላዊ ጭፈራ (ውዝዋዜ) ጠቅለል ያለ ሀሳብ ጻፉ፡፡

## 🗝 ቃላት

፩. የሚከተሉትን የባህላዊ መሳሪያ መጠሪያዎች ከስዕላቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ. ከበሮ |
| 2.  | | ለ. ዋሽንት |
| 3.  | | ሐ. መለከት |
| 4.  | | መ. ማሲንቆ |
| 5.  | | ሠ. ክራር |

## ምዕራፍ ስድስት

፪.የሚከተለውን የልጆች መዝሙር በሚገባ በማንበብ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ጨረቃ ድንቡል ዶቃ
አጤ ቤት ገባች አውቃ
አጤ ቤት ያሉት ልጆች
እንክርዳድ ፈታጊዎች
ፈተጉ ፈታተጉ
በጭልፋ አስቀመጡ
ጭልፋዋ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጡ
አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ይህችን ትተሽ ያችን ቶሎ

ምሳሌ፡- ገባች እና ልጆች

1. ________ እና ________
2. ________ እና ________
3. ________ እና ________
4. ________ እና ________
5. ________ እና ________

፫. የሚከተሉትን ሆሄያት በሳጥኑ ውስጥ ካሉት ቃላት ጋር በማዋሃድ ከፊደሉ ጎን ፃፉ፡፡

1. ጨ፡- ________ ፣ ________
2. ጠ፡- ________ ፣ ________
3. መ፡- ________ ፣ ________

| | |
|---|---|
| ጨመረ | መሰንቆ |
| መረጠ | ጠበቀ |
| ጠፈር | ጨረቃ |

## መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቱን በሚገባ በማንበብ በምሳሌው መሰረት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የተለያዩ = የ-ተለያዩ

ከባህል = ከ-ባህል

1. ከእንጨት፡- ____________
2. የመሳሪያ፡- ____________
3. የሚሰራ፡- ____________
4. ከሸንበቆ፡- ____________
5. በከብት፡- ____________

፪. የሚከተለውን ፅሑፍ በማንበብ ፅሑፉን የሚወክለውን ፊደል ፃፉ፡፡

### እኔ ማን ነኝ...?

እስክስታ የምመታ ሰው እመስላለሁ፡፡ በ “ሸ” እና በ “በ”መካከል እገኛለሁ፡፡ በርካታ ቃላት ይመሰርቱብኛል፡፡ በፊደል ገበታ በዘጠነኛው መስመር ላይ እገኛለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ...?

## 🕮 ንባብ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ከትምህርታችሁ ጎን ለጎን ምን ምን ክበባት ላይ ትሳተፋላችሁ?
2. ክበባት ውስጥ ተሳትፎ የምታደርጉ ከሆነ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ?

## የባህል ቀን

ዕለቱ ሀሙስ ነው፡፡ ሜሮን ከትምህርት ቤት እንደገባች የደንብ ልብሷን ቀየረች፡፡ ወዲያውኑ ባህላዊ ዘፈኖችን ከፍታ መወዛወዝ ጀመረች፡፡ እናቷ ተደብቀው ያይዋታል፡፡ ልጃቸው የተለያዩ ውዝዋዜ መቻሏ ገርሟቸዋል፡፡ እናቷም ከልጅነት የዕድሜ ዘመናቸው ጀምሮ ባህላዊ ተወዛዋዥ በመሆን ያገለገሉ በመሆናቸው በትዝታ ተዋጡ፡፡ ድንገት ሜሮን "እማዬ" ብላ ተጣራች፡፡ እናቷም "አቤት ልጄ" አሏት፡፡ "ነገ በትምህርት ቤታችን የባህል ቀን ይከበራል፡፡ 'ሁላችሁም የተለያዩ ባህላዊ ልብሶች ልበሱ፤ ባህላዊ ጭፈራዎችንም ተለማመዱ፡፡' ተብለናል፡፡" አለቻቸው፡፡

የሜሮን እናት በሜሮን ድርጊት የሚደሰቱ ይመስላችኋል?

እናቷም “ጥሩ ነው! ባህላዊ ሙዚቃዎቻችንና ባህላዊ ጭፈራዎቻችንን በሚገባ ማወቅ አለብን። እኛ ያወቅነውን ለእናንተ እናስተላልፋለን፤ እናንተ ያወቃችሁትን ደግሞ በመጨመር ለቀጣይ ትውልድ ታስተላልፋላችሁ። ይህ ሲሆን ባህላችን እንደተጠበቀ ይቀጥላል። ስለዚህ ቀድም ስትወዛወዢ እያየሁሽ ነበር፤ የተሳሳትሻቸው እንቅስቃሴዎች አሉ።” በማለት ማስተካከያ ሰጧት። ሜሮንም ትምህርት ቤት ሄዳ የባህል ቀን ላይ ጥሩ ውዝዋዜ አቀረበች። ባቀረበችውም ውዝዋዜ ተመልካቾች ስለተደሰቱ በሽልማት አንበሻበሿት።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት ሆኑትን ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።

1. የሜሮን እናት የባህላዊ ሙዚቃ ተወዛዋዥ ነበሩ።
2. በእነሜሮን ትምህርት ቤት የሚከበረው የሴቶች ቀን ነበር።
3. የሜሮን ችሎታ(ተሰጥኦ) ሥነ ፅሑፍ ማዘጋጀት ነው።

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች “የባህል ቀን” የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

## ቃላት

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ "ሀ" ስር ያሉትን በ "ለ" ስር ካሉት ጋር እንደአገባባቸው አዛምዱ።

| ሀ | መልስ | ለ |
|---|---|---|
| 1. ውዝዋዜ | | ሀ. ታዳሚ |
| 2. ጥሩ | | ለ. መልካም |
| 3. ተመልካች | | ሐ. እስክስታ |
| 4. ትዝታ | | መ. ልማድ |
| 5. ባህል | | ሠ. ትውስታ |

፪. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- /ዘ/ ሀ፡- ዘፈነ

ለ፡- ዘመረ

1. /ከ/ ሀ፡- __________
ለ፡- __________

2. /በ/ ሀ፡- __________
ለ፡- __________

3. /መ/ ሀ፡- __________
ለ፡- __________

፫. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ክራር እና ብድር

1. ሀ፡- __________
ለ፡- __________

2. ሀ፡- __________
ለ፡- __________

3. ሀ:- ____________
   ለ:- ____________

፬. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት መድቧቸው::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ከበሮ | ጊታር | ፒያኖ | በገና | ማንዶሊን |
| ማሲንቆ | ክራር | ሳክስፎን | ዋሽንት | ኪቦርድ |

| ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ✍ ጽሕፈት

፩. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች በሚገባ በማዳመጥ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ::

፪. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በሚገባ በማንበብ በሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም አሟሉ::W

| ? | ! |
|---|---|

1. ስንት ሰዓት ነው
2. የሜዳው ሳር በጣም ደስ ላል
3. የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያው ድምፅ ይማርካል
4. ባህል ማለት ምን ማለት ነው

፫. ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራት በጋራ ሆናችሁ ስሩ፡፡

ሀ. በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተቀመጡ፡፡

ለ. ባህላዊ ሙዚቃን በተመለከተ ሁላችሁም የየራሳችሁን ሶስት ሶስት ጥያቄዎች ፃፉና እርስ በርስ ተቀያየሩ፡፡

ሐ. ላወጣችኋቸው ጥያቄዎች በጋራ በመሆን በፅሁፍ ምላሽ ስጡ፡፡

መ. በጋራ በመሆን ላወጣችኋቸው ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ላይ ተነጋገሩ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቱን በሚገባ በማንበብ የመጀመሪያ ፊደላቸውን ከቃሉ በመነጠል ጻፉ፡፡

ሀ. የጭፈራ

ለ. ለሙዚቃ

ሐ. በሥርዓት

መ. ከሰርግ

ሠ. በእንቢልታ

ረ. የነጋሪት

፪. የሚከተለውን ተግባር በአጠያየቁ መሰረት መልሱ፡፡

እስኪ አወቁኝ...?

ከእንጨት የምሰራ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነኝ፡፡ ቁመቴ ረጅም ነው፡፡ በውስጤ አስር አውታሮች (ክሮች) አሉኝ፡፡ ለስለስ ያለ ድምፅ ስለማወጣ በርካታ ሰዎች ይወዱኛል፡፡ ብዙ ጊዜ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እውላለሁ፡፡በአንዳንድ መንፈሳዊ በዓላት ላይ እገኛለሁ እኔ ማን ነኝ...?



አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
## መልካም ስነ ምግባር

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከአመጣችሁት ፅሑፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓ.ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በተገቢ ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ታነባላችሁ፡፡
- የተሰጣችሁን ቃላት በትክክል ትፅፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

# ትክክለኛ ዳኛ



## ቅድመ-ማዳመጥ

1. በምትማሩበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲጣሉ ምን ታደርጋላችሁ?
2. ከላይ የቀረበውን ምስል በትኩረት በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት የሆኑትን ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ዳኛው ከፍትህ ይልቅ ለወዳጅነት ያደላል፡፡
2. ለጓደኛ ማዳላት የትክክለኛ ዳኛ መገለጫ ነው፡፡
3. አቶ በልሁ የፍርድ ቤት ዳኛ ናቸው፡፡
4. ዳኛው መልካም ስነ ምግባር ያለው ነው፡፡

፪. መምህራችሁ ያነበቡላችሁ ምንባብ ውስጥ ባሉ ቃላት አምስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሲራጅ የቅርብ ወዳጄ ነው፡፡

## ቃላት

፩. የአዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ በ”ሀ” ስር የቀረቡትን ቃላት ከ”ለ” ስር ካሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እውነተኛ | ሀ. ጠላት |
| 2. ማዳላት | ለ. ሐሰተኛ |
| 3. ወዳጅ | ሐ. ጽድቅ |
| 4. ሐጢአት | መ. ሚዛናዊነት |
| 5. ክብር | ሠ. ውርደት |

፩. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በትኩረት በማንበብ ተመሳሳይ የመድረሻ ፊደል ያላቸውን ቃላት በተሰጡት ምድቦች አስቀምጡ፡ ፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በላች | የዋህነት | አየች | ጫማዎች | ተማሪዎች |
| ገበሬዎች | ደግነት | ቸርነት | ሰራች | |

| በ"ች" የሚጨርሱ | በ"ዎች" የሚጨርሱ | በ"ነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

በምሳሌው መሰረት በክቡ ውስጥ ያለውን ቃል ከሌሎቹ ቃላት ጋር አጣምሩ፡፡




ሀ. መልካም ሰው

ለ. መልካም ምግባር

ሐ. መልካም ስራ

መ.__________

ሠ.__________

ረ.__________


ሰ.__________

## 📖 ንባብ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ፊደል የት እንደተማራችሁ ታስታውሳላችሁ?አዎ ካላችሁ ምን ምን ነገሮችን እንደምታስታውሱናቹ።
2. በምስሉ ላይ የምትመለቷቸው ሰዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኃል?

### "ሀሁ..."



አንድ ትንሽ ልጅ ወደአንድ የኔታ ዘንድ ሄዶ "ሀ ሁ" ይቆጥር ነበር፡ ፡ ወላጆቹም እጁን ይዘው መንገድ ያሻግሩትና ከየኔታ ጋር ያገናኙታል። የኔታም ወደክፍል ያስገቡትና ፊደል እንዲቆጥር ያደርጉታል። አንድ ቀን ይሄው ተማሪ እያለቀሰ ወደቤቱ መጣ። አባቱም "ምነው? ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው?" ሲሉ ይጠይቁታል።

ልጅ፡- “የኔታ ተቆጡኝ!”

አባት፡- “መቼም ሳታጠፋ ዝም ብለው አይቆጡህም፤ በል እውነቱን ንገረኝ! ከዋሸህ እኔም እቀጣሃለሁ!” አሉት፡፡

ልጅ፡- “መነሻውማ “ሀ በል” ሲሉኝ ዝም ስላልኳቸው ነው!” አለ፡፡

አባት፡- ተናደዱና “አንተ እንዴት ዝም ትላለህ? ‘ሀ’ ማለት አቅቶህ ነው?” ብለው በንዴት ጠየቁት፡፡

ልጅ፡- “አይ አባዬ አላቃተኝም፤ ግን እሱን ብቻ አይጠይቁም፡፡”

አባት፡- “እና ምንድን ነው የሚጠይቁህ?”

ልጅ፡- ‘’ ‘ሀ’ ስትል ‘ሁ’ በል ይሉሃል፡፡ ‘ሁ’ ብዬ ተገላገልኩ ስትል ‘ሂ’ በል ይሉሃል፡፡ እንዲህ እያሉ እስከ ‘ፐ’ ያስለፈልፉሃል! አያድርስብህ አባዬ!” አለና መለሰ፡፡

አባት፡- በልጁ ስንፍና ደነገጡ! “ልጄ ያንተኮ ስራ መማር ነው፤ የኔታ ደጋግመው የሚያስተምሩህ ጥሩ እውቀት እንዲኖርህ ነው፤ ስለዚህ ከነገ ጀምሮ በርትተህ መማር አለብህ፡፡” ብለው መከሩት፡፡ ልጁም የአባቱን ምክርና የመምህሩን ትምህርት ተቀብሎ ጎበዝ ተማሪ ሆነ፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ትንሹ ልጅ የኤታ ጋር እንዲሄድ የተደረገው ለምንድን ነው?
   ሀ. እንዲረብሽ ለ. እንዲማር ሐ. እንዲሰለች
2. ልጁ ከተመከረ በኋላ ምን ሆነ?
   ሀ. ሰነፍ ተማሪ ለ. ስልቹ ተማሪ ሐ. ጎበዝ ተማሪ
3. በምንባቡ ውስጥ "ተገላገልኩ" የሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺ ምንድን ነው?
   ሀ. ጨረስኩ ለ. ጀመርኩ ሐ. ደከመኝ

፪. ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ "ሀሁ…" የሚለውን ምንባብ ዋና ሐሳቡን በአጭሩ ፃፉ፡፡

## ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጡ፡፡

1. መማር
2. ጥበቃ
3. መንገድ
4. እውቀት
5. ምክር

፪. በ"ሀ" ስር ያሉትን ምልክቶች ከ"ለ" ስር ካሉት ስያሜያዎቻቸው (መጠሪያዎቻቸው) ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. | X | ሀ. ማካፈል |
| 2. | ÷ | ለ. ማባዛት |
| 3. | + | ሐ. መቀነስ |
| 4. | - | መ. እኩል ይሆናል |
| 5. | = | ሠ. መደመር |

፫. የሚከተሉትን ምልክቶች ከዓረፍተ ነገሮቹ ጋር በማጣጣም አገናኙ።

| x<br>አብዛ | +<br>(ጨምር) | -<br>(ቀንስ) | ÷<br>(አካፍል) | =<br>(እኩል) |
|---|---|---|---|---|

1. መልካምነትህን ______________ አብዛ።
2. ያለህን ለሌለው ______________ ።
3. ደግነትና የዋህነትን ______________ ።
4. ስንፍናን ______________ ።
5. ለሁሉም ________ አመለካከት ይኑርሽ።

## አቀላጥፎ ማንበብ

"ሀሁ…" የሚለውን ምንባብ በተገቢው የአነባበብ ስልት ደጋግማችሁ በማንበብ እንደአባትና ልጅ በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አቅርቡላቸው።

## ✍ጽሕፈት

፬. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ ጻፉ።

1. ደግ፡-______________
2. ሰነፍ፡-______________
3. ጥሩ፡-______________
4. ውሸት፡-______________
5. ምርቃት፡-______________

፪. በተሰጣችሁ ሰንጠረዥ መልካም ምግባር እና መጥፎ ምግባር የሚባሉትን ተግባራት በየምድባቸው ፃፉ፡፡

| መልካም ምግባር | መጥፎ ምግባር |
|---|---|
| ሠውን መርዳት | መስረቅ |
| 1. | 1. |
| 2. | 2. |
| 3. | 3. |

፫. በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡

ምሳሌ፡- ጓደኛ፡- የብርቱካን ጓደኛ ታማኝ ናት፡፡

ዳኛ፡- አቶ ሲራጅ ዳኛ ናቸው፡፡

1. ፍርድ ቤት፡-______________________________
2. መከባበር፡- ______________________________
3. ትህትና፡-______________________________
4. መታዘዝ፡-______________________________
5. ደግነት፡-______________________________

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በትኩረት በማንበብ ተመሳሳይ የመድረሻ ፊደል ያላቸውን ቃላት በተሰጡት ምድቦች አስቀምጡ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| መጣን | አነበብን | በላህ | ገዛህ |
| | ተኛህ | | |
| መልካምነት | ልጅነት | በጎነት | ሰጠን |

| በ"ን" የሚጨርሱ | በ"ህ" የሚጨርሱ | በ "ነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

## ፪. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. መርዳት፡- ________________________
2. አረጋውያን፡- ________________________
3. ምግባር፡- ________________________
4. መተባበር፡- ________________________
5. ጥላቻ፡- ________________________

# ምዕራፍ ስምንት
## የምግብ አዘገጃጀት

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ታደራጃላችሁ፡፡
- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ከምንባብ ውስጥ ተራ ዓረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ተጋቢኖ



### ቅድመ-ማዳመጥ

1. ተማሪዎች በቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ምግቦችን ታዘጋጃላችሁ?
2. በቤታችሁ ውስጥ ከሚዘጋጁ ምግቦች አንዱን መርጣችሁ

   አሰራሩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### አዳምጦ መናገር

፩. ℇሚከተሉትን ጥ¦ቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት የሆኑትን ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ብሩክ የሰራው ዶሮ ወጥ ነው፡፡
2. ተጋቢኖ  ለመስራት የግድ ዘይት ያስፈልጋል፡፡
3. የብሩክ እናት የሄዱት ሰርግ ነው፡፡

፪. የምንባቡን ታሪክ በቅደም ተከተል በማምጣት በዓ.ነገር አስቀምጡ።

| | |
|---|---|
| መጀመሪያ | ብሩክ እናቱ ለቅሶ ስለሄዱ ወጥ አልቆበት ራበው። |
| ከዚያ | |
| በመቀጠል | |
| በመጨረሻ | ብሩክ ምሳውን ከእናቱ ጋር በላ። |

ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

| ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ጠዋት | |
| 2. በልቶ | |
| 3. አይቼ | |
| 4. መጠነኛ | |
| 5. ከለሰ | |


፪. የሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡- ስለበላ = ስለ-በላ ወደቤት = ወደ-ቤት

1. እንደፃፈ፡- ________
2. የተቀባ፡- ________
3. ከሰራ፡- ________
4. ስለጠጣ፡- ________
5. ለእናት፡- ________

# ምዕራፍ ስምንት

## ፫. የሚከተሉትን ስዕሎች ከመጠሪያቸው (ከስማቸው) ጋር አዛምዱ።

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1  | | ሀ. ቆስጣ |
| 2  | | ለ. ድንች |
| 3  | | ሐ. ሙዝ |
| 4  | | መ. ፓፓዬ |
| 5  | | ሠ. በቆሎ |

## 📖 ንባብ



### ቅድመ ንባብ

1. የተመጣጠነ ምግብ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. የተመጣጠነ ምግብ ለምን ይጠቅማል?

## የተመጣጠነ ምግብ

ለሰው ልጆች ከሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ምግብ ነው፡፡ ምግብ የሰው ልጆች ጤነኛና ጠንካራ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ የሰው ልጆች ደግሞ ጤነኛና ጠንካራ የሚሆኑት የተመጣጠነ ምግብ ሲያገኙ ነው፡፡

የተመጣጠነ ምግብ የምንላቸው ከእንስሳት ተዋፅኦ፣ ከተክሎች፣ ከፍራፍሬ ውጤቶች፣ ከአዝዕርት ምርቶች… የሚገኙትን ነው፡፡ የሰው ልጅ ከእነዚህ ውጤቶች በየዕለቱ ማግኘት ከቻልን ጠንካራና ጤነኛ ይሆናል፡፡

ተማሪዎች ከእንስሳት ምን ምን ምግቦችን እናገኛለን ?

ከእንስሳት ተዋፅኦ የሚገኙት እንደቅቤ፣ ወተት፣ እንቁላል፣ ስጋ… ወዘተ ናቸው፡፡ ከአትክልቶች እንደ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣

ጎመን፣ ቆስጣ... ይገኛሉ። ከፍራፍሬ ውጤቶች ደግሞ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ...ይመደባሉ። ከአዝእርት ምርቶች ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ...ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ግብአቶች የምናገኘው ምግብ ለሰውነታችን ኃይልና ሙቀት ይሰጣል፤ በሽታም ይከላከላል፤ ሰውነታችንን ይገነባል። ስለዚህ እነዚህን ምግቦች በአግባቡና በንፅህና በማዘጋጀት መመገብ ያስፈልጋል።

## አንብቦ መረዳት

### ፩. £ሚከተሉትን ጥ¦ቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. የተመጣጠነ ምግብ ለጤና አስፈላጊ ነው።
2. በምንባቡ ውስጥ አምስት አራት ነጥቦች ብቻ አሉ።
3. የሰው ልጆችን ጤነኛና ጠንካራ የሚያደርጋቸው ምግብ ነው።

## ቃላት

### ፩. የሚከተሉትን ቃላት በየመደባቸው አስቀምጡ።




ጎረሰች ረጅም ተጋቢኖ ወጥ በላ ቀጭን
ዳቦ እንጀራ ወፍራም ጠጣ ሰራች አጭር

| ድርጊት የሚያሳዩ | የምግብ መጠሪያ | መጠንን የሚገልፁ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

፱. በ"ሀ" ስር ያሉትን በ"ለ" ስር ከሚገኙት ተስማሚ ቃላት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ምጣድ | |
| 2. ማማሰያ | |
| 3. ጭልፋ | ሀ. ለእንጀራ |
| 4. ድስት | ለ. ለወጥ |
| 5. መሶብ | |
| 6. ሰፌድ | |

፲. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን የድርጊቶች ምስሎች ከመጠሪያቸው ጋር አዛምዱ።

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1  | | ሀ. መግመጥ |
| 2  | | ለ. መብላት |
| 3  | | ሐ. መጠጣት |
| 4  | | መ. መክተፍ |
| 5  | | ሠ. መቁረጥ |

## ✍ጽሕፈት

፩. የተመጣጠነ ምግብ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ሶስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

፪. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

1. መክተፊያ፡-______________________________

2. ማንቆርቆሪያ፡-____________________________

3. ቢላዋ፡-__________________________________

፫. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ታሪክ መሰረት በማድረግ አንድ የምታስታውሱትን በዓል መርጣችሁ ታሪክ ፃፉ።

- ስትፅፉ የሚከተሉትን ጉዳዮች አካቱ፡-

  ሀ. የበዓሉ ስም፣ ቦታ እና ጊዜ

  ለ. በበዓሉ ላይ ያጋጠማችሁ ገጠመ

  ሐ. በዓሉ የተጠናቀቀበት ሁኔታ...

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ተስማሚ የሆኑ ቃላትን በመፈለግ አጣምሩ።

ምሳሌ፡- ልብስ፡- ልብስ ሰፊ

1. ፀጉር፡- ____________
2. ዶሮ፡- ____________
3. መዝሙር፡- ____________
4. ቀለም፡- ____________
5. ዜና፡- ____________

፪. በሰንጠረዡ ውስጥ የተለያዩ ፊደላት ቀርበዋል፤ ፊደሎችን ወደላይ፣ ወደታች፣ ወደጎን እንዲሁም አግድም በማገናኘት ቃላትን መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መ | ጋ | ዝ | ቅ | ጂ |
| ጥ | ዘ | ን | ባ | እ |
| ረ | ሃ | ብ | ት | ህ |
| ጊ | ታ | ር | ጉ | ል |
| ያ | ቤ | ተ | ሰ | ጠ |

# ምዕራፍ ዘጠኝ
## ዲጅታል ቁስ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከአዳመጣችሁት የምንባብ ጽሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ታደራጃላችሁ፡፡
- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ታነባላችሁ፡፡
- ዓረፍተ ነገር በትክክል ትጽፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### መረጃ ማግኛ ቁሶች




### ቅድመ-ማዳመጥ

1. መረጃ ማግኛ ቁሶች የሚባሉት እነማን ናቸው?
2. ከላይ የቀረበውን ምስል በትኩረት በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ::

### አዳምጦ መናገር

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ::**

1. የድሮው የመረጃ ልውውጥ ከአሁኑ በምን ይለያል?
2. መረጃን በፍጥነትና በሁሉም ቦታ ለማድረስ የሚያገለግሉ ዲጂታል ቁሶችን ዘርዝሩ::
3. በዲጅታል ቁሶች ህይወትን የምናቀለው እንዴት ነው?

፪. የመረጃ ማግኛ ቁሶችን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ ቡድን መስርታችሁ ተወያዩ። የተወያያችሁትን ሀሳብ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ቃላት

፩. የሚከተሉትን ቃላት ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ፍቺ ስጡ።

1. ቁስ፡-________________
2. ማስተሳሰር፡-________________
3. ማዳረስ፡-________________
4. መረጃ፡-________________
5. ልውውጥ፡-________________

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ. ካሜራ |
| 2.  | | ለ. ቴሌቪዥን |
| 3.  | | ሐ. ላፕቶፕ |
| 4.  | | መ. ሞባይል |
| 5.  | | ሠ. ራዲዮ |

## 🕮 ንባብ



### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. እቤት ስትሆኑ ብዙ ጊዜያችሁን የምታሳልፉት ምን በመስራት ነው?
2. ምስሉን አይታችሁ የምታነቡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

## የጊዜ ብክነት

ጊዜው በጣም መሽቷል፡፡ አባት የሆነ ድምጽ ሲሰማ ከእንቅልፉ ነቃ፤ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ከምሽቱ አምስት ተኩል ሆኗል፡፡ የምን ድምጽ እንደቀሰቀሰው ለማወቅ ከመኝታ ቤቱ ወጣ፡፡ መንክርን ስልኩ ላይ አፍጥጦ "ጌም" ሲጫወት አገኘው፡፡ አባቱም የልጁን ድርጊት በግርምት ተመለከተ፡፡ መለስ ብሎ በሀሳቡ የመንክርን ውሎ መመርመር ጀመረ፡፡

መንክር ከትምህርት ቤት እንደተመለሰ የቀረበለትን ምግብ እንደነገሩ ቀማምሶ ቴሌቪዥኑን ከፈተው፡፡ የአሻንጉሊት ፊልም ሲያይ የእራት ሰዓት ደረሰ፡፡ እራቱን ጥቂት በልቶ የአባቱን ስልክ ይዞ ወደክፍሉ ገባ፡፡ ከክፍሉ ከገባ ጀምሮ አባቱ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ "ጌም" እየተጫወተ ነበር፡፡ አባቱም ልጁን እንደተመለከተ በዚያ ምሽት ምንም ነገር መናገር ስላልፈለገ እንዲተኛ ነግሮት ወጣ፡፡

| አባቱ በልጁ ድርጊት የተደሰተ ወይስ የተከፋ ይመስላችኋል? |
|---|

ነጋ፡፡ የመንክር አባት ቀድሞ ተነሳና ቁርስ ሰራ፡፡ እናትም በመነሳት ቤቱን ማስተካከል ጀመረች፡፡ መንክር ግን አልተነሳም ነበር፡፡ አባትም መንክርን በመቀስቀስ ስለኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አጠቃቀም መምከር ጀመረ፡፡ እናትም "ልጄ ሙሉ ትኩረትህን ስልክና ቴሌቪዥን ላይ በማድረግህ ምግብ ለመብላትም ጊዜ አጥተሀል፡፡

በተጨማሪም የተማርከውን የምታነብበት፣ የቤት ሥራም የምትሰራበት ጊዜ ያስፈልግሀል። ስልክም ሆነ ቴሌቪዥን በአግባቡና በተወሰነ ጊዜ ከተጠቀምንበት ጠቃሚ ሲሆን ከልክ በላይ ከተጠቀምንበት ግን ጎጂ ነው።" በማለት የራሷን ምክር ጨመረች። መንክርም የእናቱንና የአባቱን ምክር ትኩረት ሰጥቶ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ ጥፋቱን አምኖ የተሰጠውን ምክር ተቀበለ። የእለት ክንውኑን መርኃ ግብር (ፕሮግራም) አውጥቶ ማንበብ ጀመረ።

## አንብቦ መረዳት

### ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልስ ስጡ።

1. በምንባቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዛት ስንት ነው? ማንነታቸውን ግለጹ።
2. አባትና እናት ልጁን የመከሩት መቼ ነው?
3. መንክር የእናትና አባቱን ምክር ከሰማ በኋላ ምን አደረገ?

### ፪. ካነበባችሁት ምንባብ የተረዳችሁት መልዕክት በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የቡድናችሁን ሀሳብ በጽሑፍ ግለፁ።

## ቃላት

፩. በምንባቡ መሰረት በ"ሀ" ስር ላሉት ቃላት ከ"ለ" ስር ካሉት ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|
| 1. ነቃ | | ሀ. ጠዋት |
| 2. ምሽት | | ለ. ቀነሰ |
| 3. ጨመረ | | ሐ. ተኛ |
| 4. አፍጥጦ | | መ. ብዙ |
| 5. ጥቂት | | ሠ. ጨፍኖ |

፪. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ።

1. ቀማምሶ
2. ተመለከተ
3. ቀድሞ
4. ጎጂ
5. በአግባቡ

### መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አጣማራችሁ ፃፉ።ከዚያም የተነጣጠለውንና የተጣመረውን ጥንድ ሆናችሁ በመቀባበል አንብቡ።

<table>
<tr><td rowspan="3">ስነ</td><td>ምሳሌ፡- ስነ-ስርዓት</td><td rowspan="9">ሙከራ<br>ውበት<br>ስርዓት<br>ብርሃን<br>ክርስትያን<br>ምግባር<br>መጻሕፍት<br>ደንዳና<br>ቢስ</td></tr>
<tr><td></td></tr>
<tr><td></td></tr>
<tr><td rowspan="3">ልበ</td><td>ምሳሌ፡- ልበ-ደንዳና</td></tr>
<tr><td></td></tr>
<tr><td></td></tr>
<tr><td rowspan="3">ቤተ</td><td>ምሳሌ፡- ቤተ-ሙከራ</td></tr>
<tr><td></td></tr>
<tr><td></td></tr>
</table>

፪. ከዚህ በታች ተነጣጥለው የተጻፉትን ቃላት አጣምራችሁ በመጻፍ አንብቧቸው፡፡

1. የ-ዜና፡-____________
2. ለ-መዝናኛ፡-____________
3. እየ-ተናገረ፡-____________
4. እንደ-ሄደ፡-____________
5. ተ-ገነባ፡-____________
6. ከ-መገናኛ፡-____________

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩. "የጊዜ ብክነት" የሚለውን ምንባብ በሚከተለው መንገድ አንብቡ፡፡

ሀ. ደቂቃ በመያዝ በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡

ለ. ምንባቡን እየተከፋፈላችሁ በመቀባበል አንብቡ፡፡

ሐ. ስታነቡ ለማንበብ የጨረሰባችሁን ጊዜና የተፈጠረውን ስህተት በመከታተያ ቅጽ መዝግቡ፡፡

፪. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሥርዓተ ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በትክክል አንብቡ፡፡

ሀ. ኤች አይ ቪ ኤድስ በደም ንክኪ ይተላለፋል፡፡

ለ. የቤት ሥራ ሳትሰራ እንዳትመጣ!

ሐ. ህጻናት ትምህርት ቤት የሚገቡት በስንት ዓመታቸው ነው?

## ጽሕፈት

፩. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተ ነገሮች በማዳመጥ በትክክል ደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

፪.ባለፈው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ከተማራችሁት ትምህርት ውስጥ ሁለቱን ተግባር በአራት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባር

የሚከተለውን ፅሑፍ በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ እና የሚጨርሱ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ።

እቴሜቴ ሎሚ ሽታ፣
ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ፣
ምንም ምንም ምንም
አላለኝ፣
ትዳሩን ፈትቶ ልውሰድሽ
አለኝ፣

አይወስድሽም ትዳሩን ፈትቶ፣
ምሎልሻል ጋሻ ጦር ደፍቶ፣
ማላ ማላ የጎበዝ ማላ፣
ፉት ይላታል እንደ ጉሽ ጠላ።

| በተመሳሳይ ፊደል የጀመሩ ቃላት | | በተመሳሳይ ፊደል የጨረሱ ቃላት | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- እንደ እና እቴሜቴ | | ምሳሌ፡- ማላ እና ጠላ | |
| 1. | | 1. | |
| 2. | | 2. | |
| 3. | | 3. | |
| 4. | | 4. | |
| 5. | | 5. | |

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
## የዱር እንስሳት

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዋናውን መልዕክት በጽሑፍ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- የምንባቡን ሐሳብ ከተጨባጭ ህይወታችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ትጠቀማላችሁ፡፡
- አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ለደረጃው የሚመጥን ዓረፍተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ብልኋ ዝንጀሮ



## ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች በምትኖሩበት አካባቢ እንስሳት ጉዳት ደርሶባቸው ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?
2. ብልህ የሚለው ቃል ፍቺው ምንድን ነው?

## አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. እነዘምዘም ትንሿን ዝንጀሮ ለመርዳት ያነሳሳቸው ማን ነው?
2. እናት ዝንጀሮ የወሰደችው ህፃን ስም ማን ይባላል?
3. እናት ዝንጀሮ ልጇን ባታገኝ የወሰደችውን የሰው ልጅ ምን የምታደርገው ይመስላችኋል?

፪. "ብልኋ ዝንጀሮ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ አገባባዊ(አውዳዊ) ፍቺ ስጡ።


| ቃላት | ዐውዳዊ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ቅጠል | የረገፈ የዛፍ አካል |
| 2. የሰፈሩ | |
| 3. ወላጆች | |
| 4. መደናገጥ | |
| 5. ወጥታ | |
| 6. ወተት | |

፪. የሚከተሉትን ቃላት የመጀመሪያ ፊደል በማጥፋት በምትኩ ሌላ ፊደል በመጨመር ቃል መስርቱ።

ምሳሌ:- ጠጣ :- መጣ
ነብር :- ክብር

1. ጅብ:- __________
2. በሬ:- __________
3. ቀበሮ:- __________
4. ጉሬዛ:- __________
5. ግመል:- __________

፫. በ"ሀ" ስር ያሉትን የእንስሳት ምስሎች በ"ለ" ስር ካለው መጠሪያቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ ምስሎች | መልስ | ለ መጠሪያ |
|---|---|---|
|  1. | | 1. ቀጭኔ |
|  2. | | 2. ዝንጀሮ |
|  3. | | 3. የሜዳ አህያ |
|  4. | | 4. ዝሆን |
|  5. | | 5. አንበሳ |

# ንባብ



## ቅድመ ንባብ

1. ተማሪዎች ጦጣ የዱር ወይስ የቤት እንስሳ ናት?
2. ስለ ጦጣ የምታውቁትን እውነታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

## ጦጣ

ጦጣ በመላው ኢትዮጵያ በበርካታ ቦታዎች ትገኛለች። የብልጠት ምሳሌ ሆናም በብዙ ተረቶች ውስጥ ትጠቀሳለች። ፊቷ ጥቁር ነው። ዙሪያውን በነጭ ፀጉር የተከበበ ነው። ፀጉሯ ከግራጫማ ጀምሮ እንደየስፍራው እስከ ቡናማ አረንጓዴ ነው። ወንዶቹ በአማካይ 5.5 ኪሎ ግራም ሲመዝኑ፤ ሴቶቹ ደግሞ 4 ኪሎ ገደማ ይመዝናሉ። ጅራታቸው ረጃጅም ነው።

ርዝመታቸው ጅራታቸውን ሳይጨምር ከ45 እስከ 83 ሴንቲ ሜትር ይሆናል፤ ጅራታቸው ደግሞ ከ55 እስ 114 ሴንቲ ሜትር ይሆናል

ተማሪዎች ጦጣዎች ምን ምን የሚመገቡ ይመስላችኋል?

የጦጣዎች አኗኗር በቡድን ነው፡፡ በአንድ ቡድን ያሉ ጦጣዎች በመልክ እና በድምፅ ይተዋወቃሉ፡፡ በተጨማሪም በድምፅና በሰውነታቸው አኳኋን መልዕክት ይለዋወጣሉ፡፡ በየጊዜው የሚለዋወጠው የጅራታቸው ቅርፅ የሚያስረዳው ጉዳይ አለው፡፡

ጫፉ ወደፊት ሲያመለክት በራሱ የመተማመን ምልክት ነው፤ ወደ ኋላ ሲያመለክት ደግሞ የመፍራት ምልክት ነው፡፡

በድምፅ መልዕክት ይለዋወጣሉ፤ እነሱን ሊያጠቃ የመጣ ጠላት ካለ እንደ ጠላታቸው ዓይነት ድምፃቸውን በመቀየር ይግባባሉ፡፡ ሁለት ጦጣዎች ሲገናኙ በወዳጅነት ከሆነ ማለትም ለማከክ፣ ለመጫወት፣ ለመላፋት ወዘተ አፍንጫ ለአፍንጫ ይነካካሉ፡፡

አብዛኛዎቹ ጦጣዎች የሚወልዱት በዓመት አንድ ጊዜ ነው፡ ፡ልጆቻቸውንም እያጠቡና እየተንከባከቡ ያሳድጋሉ፡፡ጦጣዎች የሚበሉት የተገኘውንና በብዛት ያለውን ምግብ ነው፡፡

ለምሳሌ ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ፣ ቅጠላቅጠል፣ ሳሮች፣ ትላትሎች፣ እንሽላሊቶች፣ እንቁላልና በጎጆ ውስጥ ያሉትን አዕዋፍን ይመገባሉ፡፡

ጦጣዎች ብዙ ጠላት አላቸው፤ ጭልፊት፣ የሎስ፣ ነብር፣ አነር፣ ከጠላቶቻቸው ጥቂቶቹ ናቸው።

## አንብቦ መረዳት

**፩ ፪ሚከተሉትን ጥ¦ቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በፅሁፍ መልሱ።**

1. ጦጣዎች የቤት እንስሳት ናቸው።
2. የጦጣ የጅራት ቅርፅ ወደኋላ ካመለከተ የጦጣውን በራስ የመተማመን ሁኔታ ያሳያል።
3. ጦጣዎች አትክልት ብቻ ተመጋቢ እንስሳት ናቸው።

## ቃላት

**፩. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመጠቀም የተለያዩ የዱር እንስሳትን ስሞች ፃፉ።**

| የተዘበራረቁ ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት | |
|---|---|---|
| ድ ዝ ል ጣ ሮ<br>ብ ን በ ሆ ጦ<br>ዋ ር ላ ቀ ጅ<br>ኩ ጀ ኔ ነ ዝ<br>ያ ጭ | ጦጣ | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ፪.የሚከተሉትን ፊደላት በመጠቀም የተለያዩ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ጠ፡- ጠርሙስ፣ ጠረጴዛ፣ ጠነከረ...

1. ከ፡- ____________ ፣ ____________ ፣ ____________
2. ቀ፡- ____________ ፣ ____________ ፣ ____________
3. መ፡- ____________ ፣ ____________ ፣ ____________
4. አ፡- ____________ ፣ ____________ ፣ ____________
5. ደ፡- ____________ ፣ ____________ ፣ ____________

## አቀላጥፎ ማንበብ

“ጠጣ” የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡላቸው።

## ጽሕፈት

መምህራችሁ በሰሌዳ ላይ የፃፉላችሁን ዓረፍተ ነገሮች ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን በማካተት ጻፉ።

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. ከዚህ በታች የቀረበውን ፅሑፍ አንብባችሁ ምላሻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

> **እኔ ማን ነኝ?**
> በጣም ጠንካራ ነኝ። ጥንካሬዬን የማገኘው በተወለድኩ በሶስተኛው ቀን የአባቴን ድምፅ ስሰማ ነው። የእንስሳት ንጉስም እባላለው። ኩሩ እንስሳ ነኝ። በእርጅና ዘመኔ ጉልበቴ ይደክማል። በአመጋገብ ስርዓቴ ግን ጥንቁቅ ነኝ። የሞተ ነገርና ህፃናትን አልመገብም። ስተኛ ዓይኔን የማልጨፍን የዱር እንስሳ ነኝ። እኔ ማን ነኝ...?

፪. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከምታቋቸው ሰዎች ጠይቃችሁ ወይም ከመጻሕፍት አንብባችሁ ስለአንድ የቤት እንስሳ ባህርይ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

፫. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የእንስሳ ስሞች የቤት እና የዱር በማለት ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶሮ | ድኩላ | ድመት | ላም | የሜዳ አህያ |
| ሰጎን | በሬ | ቀበሮ | ዝሆን | በግ |

## ዋቢ ጽሑፎች


ሰለሞን ይርጋ። (2000)። <u>አጥቢዎቹ።</u> አዲስ አበባ፣ Limited Printers::

በላይነሽ ወርቁ። (2011)። <u>ብልኋ ዝንጀሮ</u>። አዲስ አበባ፣ USAID-RED II Project

በላይነሽ የሻው እና ቢረሳው ታደሰ። (2010)። Comet Supplementary Books Series: <u>አማርኛ 3ኛ እና 4ኛ</u>። አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

በጽሐ ዓለሙ (መ/ር)። (2011)። <u>ምዕላደ ጥበብ</u>። ደብረ ታቦር፣ ከኑ ማተሚያ ቤት።

ባህሩ ዘርጋው። (2010)። <u>ዘርጋው መለስተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>። አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አታሚዎች።

አላምረው ገ/ማርያም። (2002)። <u>የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መጽሐፍ (ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች)</u>። አዲስ አበባ፣ አልታ ማተሚያ ቤት።

<u>አዲስ አድማስ ጋዜጣ። (2011)። ግንቦት፣2011</u>።

ከበደ ሚካኤል። (1999)። <u>ታሪክና ምሳሌ</u>። ኢትዮጵያ፣ ሜጋ አታሚ ድርጅት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)። (1993)። <u>አማርኛ መዝገበ ቃላት</u>። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

GPS My City. (2021). Hamle 19 Public park. Retrieved July 28, 2021. From፡ https://www.gpsmycity.com/attractions/hamle-19-public-park-44452.

## ሙዳዬቃላት

| | |
|---|---|
| ሌጦ | ለሽያጭ የተዘጋጀ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ |
| መቃ | ለመፃፊያነት የሚውል ቀለም መንከሪያ |
| መባቻ | መጀመሪያ ( ለሳምንት፣ ለወርና ለዓመት) |
| መግራት | ማስተካከል፣ ማሰልጠን |
| ሙዚየም | የተለያዩ ቅርሶች ማስቀመጫ ማዕከል |
| ማዕድ | እንጀራ ማቅረቢያ |
| ሞክሼ | አንድ አይነት መጠሪያ ያለው |
| ሰናይ | መልካም፣ ውብ፣ ደግ |
| ቁስ | መስሪያ ነገር፣ ቦታ የሚይዝ |
| ቅርስ | በቅድመ ዘመን፣ ታሪክ ወይም የተካበተ ሀብት |
| ባልንጀራ | ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ ባልደረባ |
| ብልሃት | ጥበብ፣ ዘዴ፣ ዕውቀት |
| ብራና | ከበግና (ከፍየል) ቆዳ የሚሰራ ወረቀት የሚመስል መፃፊያ |
| ብርቅዬ | ልዩ፣ በአንድ ሀገር (ቦታ) ብቻ የሚገኝ |
| ብዕር | ከመቃ፣ ከላባ የተዘጋጀ መፃፊያ |
| ተሰጥኦ | ልዩ ዕውቀት፣ ችሎታ |
| ትስስር | ውህደት፣ ተዛምዶ |
| አውታር | የበገና፣ የክራር ጅማት |

| | |
|---|---|
| እርጅና | ሽማግሌነትና አሮጊትነት፣ በእድሜ መግፋት |
| እኩይ | መጥፎ፣ ምግባረ ቢስ |
| እጀ ጠባብ | እጅጌው ጠባብና ረጅም የሆነ ልብስ |
| ከተራ | የጥምቀት ዋዜማ፣ ግደባ |
| ዋዜማ | ከዋና በዓል አስቀድሞ የሚውል ቀን |
| ውሽንፍር | ነፋስ የቀላቀለ ዝናብ |
| የኔታ | አስተማሪዬ፣ መምህሬ |
| ጀለቢያ | የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚለበስ ረጅም ቀሚስ መሰል ልብስ |
| ጠንቅ | ሰበብ፣ መነሻ፣ መዘዝ |
| ጥልፍ | በተለያዩ ጨርቆችና ልብሶች ላይ በክርና መርፌ ተወሳስቦ የሚሰራ ጌጥ |
| ጥሞና | በዝምታ፣ በጥልቀት |
| ጥጃ | እንቦሳ፣ ያላደገ የእንስሳ (የላም) ልጅ |
| ጭጋግ | ጉም፣ ጢስ የሚመስል |

# የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሳልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| ከ1 እስከ 10 | | ከ11 እስከ 19 | |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች | የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፩ | 1 | ፲፩ | 11 |
| ፪ | 2 | ፲፪ | 12 |
| ፫ | 3 | ፲፫ | 13 |
| ፬ | 4 | ፲፬ | 14 |
| ፭ | 5 | ፲፭ | 15 |
| ፮ | 6 | ፲፮ | 16 |
| ፯ | 7 | ፲፯ | 17 |
| ፰ | 8 | ፲፰ | 18 |
| ፱ | 9 | ፲፱ | 19 |
| ፲ | 10 | | |

| ከ20 እስከ 100 | | ከ200 እስከ 1000 | |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች | የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳ | 20 | ፪፻ | 200 |
| ፴ | 30 | ፫፻ | 300 |
| ፵ | 40 | ፬፻ | 400 |
| ፶ | 50 | ፭፻ | 500 |
| ፷ | 60 | ፮፻ | 600 |
| ፸ | 70 | ፯፻ | 700 |
| ፹ | 80 | ፰፻ | 800 |
| ፺ | 90 | ፱፻ | 900 |
| ፻ | 100 | ፲፻ | 1000 |

| ከ2000 እስከ 10000 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 |
| ፵፻ | 4000 |
| ፶፻ | 5000 |
| ፷፻ | 6000 |
| ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 |
| ፺፻ | 9000 |
| ፼ | 10000 |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ 2ኛ ክፍል